# የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ከመስጠት ግዴታ ጋር በተያያዘ ስለሚደረጉ የወንጀል ክርክሮች፡ አንዳንድ ምልከታዎች

**አበበ አሳመረ***

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ የገቢ ግብር አዋጁ ተሻሽሎ እና ተጠቃሎ እንዲወጣ ከተደረገበት ከ1994 ዓ.ም[1] ጀምሮ ከፍተኛ የግብር እና የታክስ ሕጐች ማሻሻያና የአፈፃፀም ለውጥ እያደረገች ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ለረዥም ጊዜ በሥራ ላይ የነበረው የገቢ ግብር አዋጅና ማሻሻያዎቹ፣ የተርን ኦቨር ታክስና ማሻሻያዎቹ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅና ማሻሻያዎቹ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከአዳዲሶቹ የግብር እና ታክስ አዋጆችና ማሻሻያዎቻቸው በተጨማሪ የግብር አሰባሰብ ስርአቱና ተቋማቱም አብረው የማሻሻያዎቻቸው እርምጃ እንዲወሰድባቸው ተደርጓል[2]፡፡

በአሰባሰብ ስርአቱ ላይ የሚፈፀሙ ጥፋቶችም የወንጀል ሐላፊነትን ሲያስከትሉ ስለሚችሉ አስቀድሞ በወንጀል ክስነት የማይታወቀው የታክስ ወንጀል አሁን አሁን ከወንጀል ክርክሮች ተርታ አንዱ ሆኖ እንዲሰለፍ ሆኗል[3]፡፡ እነዚህ አጠቃላይ የግብር እና ታክስ ማሻሻያ እርምጃዎች እንዲሁም በተለይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተፈፃሚ መሆን መንግስት በተለያዩ ዘርፎች እየወሰዳቸው ያሉ የማሻሻያ እርምጃዎች አካል ናቸው፡፡[4]

ከታክስ ወንጀሎች መካከልም አንዱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ከመስጠት ግዴታ ጋር በተያያዘ ያለው የወንጀል ሐላፊነት ነው፡፡ እስከአሁን /*ታህሣሥ* 9 *ቀን* 2005 *ዓ.ም*/ ባለው መረጃ ቁጥራቸው 110,328.00/*አንድ መቶ አሥር* ሺህ *ሶስት* መቶ *ሃያ ስምንት* /*የሚሆኑ* የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች *አሉ*:: *ከነዚህ ውስጥ ከ60* ሺ*ህ በላይ የሚሆኑት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጠቃሚዎች ናቸው*፡፡ ወደፊትም

---

* *ኤል ኤል ቢ፣ እና ቢ.ኤ. (አ.አ.ዩ) ዐቃቤ ህግ፣የህግ አማካሪ፣የህግ ጥናት ኤክስፐርት እና በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የከፊል ጊዜ መምህር ሆኖ ሰርቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የህግ አማካሪ እና ጠበቃ ሆኖ እየሰራ ነው*፡፡

1. *ለረጅም ጊዜ በስራ ላይ የነበረው የገቢ ግብር አዋጅ* በ1953 ዓ.ም *የወጣው* አዋጅ ቁጥር 173/53 *ነበር*፡፡ ይህ አዋጅ በተደጋጋሚ እየተሻሻለ ቆይቶ በመጨረሻም በአዋጅ ቁጥር 286/94 እንዲሻርና በምትኩም ይህ አዋጅ ተፈፃሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ይህም አዋጅ በአዋጅ ቁ. 608/2001 ተሻሽሏል፡፡
2. በርግጥ ተቋማዊ ለውጡ ከ94 ዓ.ም በፊትም ተጀምሮ ነበር፡፡ ፀሐፊው በአዲስ አበባ መስተዳድር የጥናት ፕሮጀክቶች ውስጥ ይሰራ በነበረበት ጊዜ በ1989 ዓ.ም ገደማ ግብር ሰብሳቢ መ/ቤቶችን ለግብር ከፋዩ ተደራሽ በማድረግ የግብር መሠረቱ (tax base) አነስተኛ ነው ወይም የግብር ክፍተቱ (tax gap) ከፍተኛ ነው በሚል የሚተቸውን የከተማው መስተዳደርን የግብር መሠረት ማስፋት ያስፈልጋል በሚል የቀበሌ ፋይናንስ ጽ/ቤቶች እንዲቋቋሙ ተደርጐ ነበር፡፡ ይህ መዋቅራዊ ለውጥ አሁንም ቀጥሎ የአዲስ አበባ መስተዳድር ገቢዎች ጽ/ቤት /የቀድሞው ፋይናንስ ቢሮ/ በፌደራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ስር ሆኗል፡፡ በዚህ መሠረትም ባለስልጣን መ/ቤቱ የአዲስ አበባ መስተዳድርን ገቢ በውክልና እየሰበሰበ ይገኛል፡፡የግብር ክፍተት ማለት ሲሰበሰብ የሚገባውና እየተሰበሰበ ባለው የግብር መጠን መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡
3. ለምሣሌ በያዝነው የ2004 ዓ.ም በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 10ኛ የወንጀል ችሎት በርካታ የታክስ ወንጀል ጉዳዮች እየታዩ ይገኛል፡፡
4. በአጠቃላይ የግብር ማሻሻያው ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ እያደረገ ያለው የሕግ፣የተቋማት፣የኢኮኖሚና ማኀበራዊ ጉዳዮች የለውጥ እርምጃዎች (Reform Measures) አካል ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው/ ለምሣሌ Amin Abdella and John clifford ;The impact of tax reform on private sector development ; November 2011; pp1

የተመዝጋቢው ቁጥር እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ተጠቃሚዎች ቁጥር እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ ሲመጣ እንደማይችል ይታመናል፡፡

በዚህ መሠረት የዚህ ጽሑፍ መሠረታዊ ትኩረት ከሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ[5] /ከዚህ በኋላ "ደረሰኝ" ወይም "የተ.እ.ታ. ደረሰኝ" በሚል ይጠቀሣል/ ከመስጠት ግዴታ ጋር በተያያዘ ያለው የወንጀል ሐላፊነትም እየጨመረ ሲሔድ የሚችልና ለሁሉም ወገን የትኩረት ጉዳይ ሆኖ ሊቀጥል እንደሚችል ይታመናል፡፡

ደረሰኝ ካለመስጠት ጋር በተያያዘ ያለው የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ በክስ ደረጃም በአዲስ አበባ ብቻ ተወስኖ የነበረው የወንጀል ክስ በአሁኑ ጊዜ በሐዋሣ[6] እና በመቀሌ[7] ተጀምሮ ፍርድ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ያሉ ሲሆን በርካታ ጉዳዮችም በክርክር ላይ መሆናቸው ይህንኑ አስተሣሰብ የሚያጠናክር ነው፡፡ ስለሆነም የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ታክስ ከፋይ ድርጅቶች እና የግል ባለሀብቶች እራሳቸውን፣ ሠራተኞቻቸውን፣ ደረሰኝ በመስጠት ሐላፊነት ላይ የሚያስቀምጧቸውን የቤተሰብ አባላትና ሥራ አስኪያጆችን ከወዲሁ ከወንጀል ሐላፊነት እንዲጠብቁ የሚረዳቸውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉና የሚከሰሱም ከሆነ፣ የክርክሩን ባህሪ በሚገባ እንዲረዱ ለማስቻል ይህን ጽሑፍ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ጽሑፉ የተዘጋጀው ፀሐፊው በክርክር ተካፋይ የሆነባቸውንና በችሎት ውስጥ ተቀምጦ የተመለከታቸውን እውነተኛ ጉዳዮች መሠረት በማድረግ፣ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ልምድ ካላቸው የህግ ባለሙያዎች ጋርም በመወያየትና በኑሮ ልማድ እውቀት የሚታወቁትን የድርጅቶች አሠራርና አደረጃጀት ባህሪና የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ስለሆነ እውነተኛውን የክርክር ባህሪ ለመረዳትና የግብር ሕጉን አስፈፃሚ የሆነውን አካል ሐሣብም ለመገንዘብ ፁሁፉ ይረዳል ተብሎ ይታመናል፡፡ ህግ የሚዳብረው ስለወጣ ሳይሆን ሲፈጸም ነው፡፡ በአፈፃፀሙም ሂደት የሚያጋጥሙ የትርጉም እና ተያያዥ ችግሮች በፍርድ፣ በትችት እና በጥናት እየተነቀሱ እና እየዳበሩ ሲሔዱ የህግ ሳይንስ ያድጋል፡፡ በዚህ ረገድም ፅሁፉ ተጨማሪ አስተዋፅኦ ሊኖረው ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

---

5. በዚህ ጽሑፍ "ደረሰኝ "የሚለው ቃል የተ.እ.ታ. ደረሰኝን ብቻ የሚያመለክት ነው፡፡አመታዊ ሽያጫቸው ከብር 100,000.00 እስከ 500,000.00 የሆኑ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የተርን ኦቨር ታክስ ደረሰኝ አስፈቅደው በማሣተም እንዲጠቀሙ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "ደረሰኝ" የሚለው ቃል እነዚህ ግብር ከፋዮች የሚሰጡትን ደረሰኝ ወይም በማናቸውም ሁኒታ ከተ.እ.ታ ደረሰኝ ውጪ የሚሰጡትን ደረሰኞች አይመለከትም፡፡

6. በሐዋሣ ከተማ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ከመስጠት ግዴታ ጋር በተያያዘ የወንጀል ክስ ተመስርቶባቸው የተፈረደባቸውና በክርክር ላይ ያሉ ጉዳዮችም እንዳሉ ፀሐፊው ከጠበቃ ቸርነት ገ/ህይወት ጋር ባደረገው ውይይት ተገንዝቧል፡፡ ፀሀፊው እራሱም ከጉዳዩ ጋር በተያያዙ በይግባኝ የመጣ ጉዳይ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ክርክር ሲደረግበት በችሎት ተቀምጦ አድምጧል፡፡

7. ፀሐፊው ለሥራ ጉዳይ በህዳር ወር 2004 ዓ.ም ወደመቀሌ ሔዶ በነበረበት ጊዜ ይህንኑ ተገንዝቧል፡፡

**2. ስለ ታክስ ወንጀሎች በጠቅላላ**

**2.1 ፅንሰ ሐሣብ**

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁ. 285/94 እና ማሻሻያዎቹ /ከዚህ በኋላ እንደየሁኔታው "አዋጁ" በሚል ይጠቀሳል/ የሚጠቀሙት ቃል "ታክስ" የሚለውን ሲሆን በሌሎች የግብር ሕጎች ላይ ደግሞ "ግብር" የሚለው ቃልም ጥቅም ላይ ውሏል::[8] በዚህ መሠረት በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ወጥ የቃላት አጠቃቀምን ለማረጋገጥ ሲባል "ግብር" ከሚለው ቃል ይልቅ "ታክስ" የሚለውን ቃል ብቻ እንጠቀማለን::[9] በአማርኛ "የታክስ ወንጀል" በሚል የሚጠሩት የወንጀል አይነቶች በእንግሊዝኛ በአብዛኛው tax offence, tax non compliance, tax evasion, tax crime tax fraud ወዘተ በሚል ይጠቀሳሉ:: ለምሣሌ ብላክስ ሎው ዲክሽነሪ የተባለው የሕግ መዝገበ ቃላት የሚጠቀመው ቃል tax evasion የሚለውን ሲሆን ይህ ቃል tax fraud ሲባል እንደሚችልም ይገልፃል::[10]

የወንጀሉ አይነት ወይም የወንጀሉ ምድብ (category of crime) በተለያየ ስያሜ ቢጠራም መሠረታዊ የወንጀሉ ይዘት ግን ተመሣሣይ ነው፡ በአጠቃላይ ታክስ ከፋዮች ለመንግስት ሊከፍሉና ሊያሣውቁ፣ ወይም ከሶስተኛ ወገን እየሰበሰቡ ገቢ ሊያደርጉ የሚገባቸውን አንድ የተወሰነ የግብር አይነት ለምሣሌ፣ የገቢ ግብር፣ የሽያጭ ታክስ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ወዘተ በሕግ በተደነገገው መሠረት በወቅቱ አለመክፈል፣ አለማሣወቅ፣ ቀንሶ መክፈል፣ መረጃን ወይም ገቢን በሙሉ ወይም በከፊል አለማስታወቅ፣የግብር መረጃ በተሣሣተ ሰነድ ማስደገፍ ወይም ሰነዶችን ማጥበርበር ፣ ግብርን ሰብስቦ ለራሱ ጥቅም ማዋል ሳይፈቀድለት ታክስ መሰብሰብ ወዘተ የታክስ ወንጀሎች በሚል ይጠራሉ::ከዚህ በተጨማሪም ከታክስ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በሕግ ለተወሰነ ጊዜ ጠብቆ አለማቆየትም የወንጀል ሐላፊነትን ሊያስከትል ይችላል::[11]

---

8 በእንግሊዝኛ tax የሚለው ቃል ቀጥተኛ ታክስ የሚባለው (direct tax) እና ቀጥተኛ ያልሆነውን(indirect tax) የግብር አይነቶች የሚገልጽ ቃል ነው:: ሁለቱን የታክስ አይነቶች ለመለየት በአማርኛ ቀጥተኛ ታክስ ለሆነው ለምሣሌ የንግድ ትርፍ "ግብር" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ሲውል እንደተጨማሪ እሴት ታክስ ላለው ቀጥተኛ ላልሆነው ግብር ደግሞ "ታክስ" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ዋለ:: ስለሆነም "ግብር" የሚለው ቃል ቀጥተኛ ግብርን የሚመለከት ሲሆን "ታክስ" ደግሞ ቀጥተኛ ያልሆነ ግብርን የሚመለከት ነው ለምሳሌ የተጠቀሱት የግብር እና ታክስ አይነቶች በዚሁ መልክ የተከፋፈሉ ለመሆኑ የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉሙሩክ ባለስልጣን ጥቅምት 2003 ዓ.ም #በሀገርዎ የግብር እና ታክስ ስርአት መሰረታዊ ጉዳዮችን ይረዱ$ በሚል ርዕስ ያሳተመውን የግንዛቤ መፍጠሪያ ብሮሸር ይመለከቷል::

9. ለምሣሌ የገቢ ግብር “income tax“ አዋጅ /አዋጅ ቁ. 286/94 "ግብር" የሚለውን ቃል ይጠቀማል::የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ደግሞ "ታክስ" የሚለውን ቃል ይጠቀማል/ አዋጅ ቁ. 587/2000 አንቀጽ 2/1/ ይመለከቷል::

10. Bryan Garner; Black’s law dictionary;8th ed. pp 1501

11. ለምሣሌ የግብር መረጃን ሆነ ብሎ አጥፍቷል በሚል የተከሰሰ ተከሣሽ «መረጃው የጠፋው በመብራት መቋረጥ ምክንያት በኮምፒዩተሩ ላይ የነበረው መረጃ በመጥፋቱ የተነሣ ነው እንጂ እኔ ሆን ብዬ ያጠፋሁት አይደለም$ የሚል የመከላከያ ጭብጥ አስይዞ የኮምፒውተር ባለሙያ የሆነ ምስክር ሲሰማ ፀሐፊው በችሎት ተቀምጦ አዳምጧል/በ2004 ዓ.ም/::በሌሎች ሃገሮችም ለምሳK? በአውስትራሊያ ከተዘረዘሩት የታክስ ወንጀሎች ጋር በተየያዘ ክስ ተመስርቶ የተቀጡ እንዳሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ ለምሳሌ http://www.ato.gov.au/corporate/content.aspx?Doc=/content/00322716.htm በሰኔ 13/2004 ኢ.ም፡ የታየ::

እነዚህን ተግባራት ተራ ወንጀል አድርጐ መውሰድ፣ እንደገንዘቡ መጠንም ቀላል ወይም ከባድ ወንጀል አድርጐ መውሰድ፣ወይም የፍትሐብሔር ጉዳይ ብቻ አድርጐ መውሰድ በየሐገሮቹ የግብር ፖሊሲ፣የወንጀል ፖሊሲ፣የዜጐች የግብር ግዴታን የማክበር ባህል (culture of tax obligation Compliance)፣መንግስት በግብር ላይ እንዳለው የጥገኝነት መጠንና[12] ሌሎች ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው::

ለምሣሌ በስዊዘርላንድ[13] እጅግ በጣም የከፋ ወንጀል ካልሆነ በስተቀር በጠቅላላ ያለው ዝንባሌ የታክስ ጥፋቶችን የፍትሐብሔር ጉዳይ ብቻ አድርጐ መውሰድ ነው:: በአሜሪካም ያለው ዝንባሌ የግብር ግዴታ ጥሰትን እንደስዊዘርላንድ ባይሆንም ወደፍትሐብሔር የመውሰድ ዝንባሌ ይታያል:: የወንጀል ጉዳይ ከሆነም ግልጽ በሆነ በአውቀ ማጥፋት የሀሳብ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት የሚል ነው:: ይህ የወንጀል ሀላፊነቱ በዚህ አስተሳሰብ ላይ እንዲመሰረት የተደረገበት ምክንያት የታክስ ሕግና አፈፃፀም በባህሪው ውስብስብና ማንም ተራ ሰው ወይም ባለሙያ ያልሆነ ሰው በቀላሉ ተረድቶት ሀላፊነቱን ሊያውቅ ይችላል ሊባል የሚችልበት ስላልሆነ የታክስ ባለሙያዎቹ ሳይቀሩ በቸልተኝነት፣ ባለማወቅ፣ ወይም የተለያየ አተረጓጐም፣ ስሌትንና አሠራርን በቅን ልቦና አምነውበት ስህተት ሲፈጽሙ ይችላሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው:: በዚህ የተነሣ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ሆነ ተብሎ የሚፈፀም የግዴታ ጥሰት (clear violation of actually known legal duty) ስለመኖሩ በበቂ ማስረጃ ካልተረጋገጠ በስተቀር የታክስ ወንጀል ሐላፊነት እንዲኖር አይደረግም::[14]

በሌላ በኩል በሀገራችን የሚታየውን የታክስ ወንጀል ክስ በተመለከተ የወንጀል ተጠያቂነትን ማስፋት ታክስ የመክፈል ወይም የታክስ ግዴታ የመወጣትን ባህል እንዲዳብር ስለሚያደርግ በተለይ ይህ ባህል ዝቅተኛ ነው ተብሎ በሚታሰብበት ህብረተሰብ የወንጀል ሐላፊነት እንዲኖር ማድረግና በዚህ መሠረትም ክሶ ማስቀጣት ተገቢ ነው በሚል የሚከራከሩ ባለሙያዎች አሉ[15]::

12. መንግስት ከማዕድንና ከነዳጅ እንዲሁም ከሌሎች ትላልቅ ኩባንያዎችና ከመሣሣሰሉት የገቢ ምንጮች የሚያገኘው ገቢ ከፍተኛ ከሆነ አነስተኛ ገብር ከፋይ ላይ የሚኖረው ጥገኝነት( dependency) ዝቅተኛ ይሆናል::

13. David f williams; Tax and corporate social responsibility; discussion paper; sept;2007

14 Definition of tax evasion; an affirmative act ; http:11en.m. wikipedi. org. በግንቦት 6/2004 ዓ.ም ¾ታ¾::የታክስ ባለሙያዎች በመባል የሚታወቁት የታክስ ህግ ባለሙያዎች፣ታክስ አካውንታንቶች፣ታክስ ኦዲተሮች እና የታክስ ኢኮኖሚስቶች ወዘተ ናቸው::

15 ለምሣሌ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ የነበረና በአሁኑ ጊዜ ጠበቃ የሆነ የሕግ ባለሙያ ይህ እምነት እንዳለው ለፀሐፊው ገልጾለታል/ለሙ እንዲጠቀስ ስላልፈለገ አልተጠቀሰም:: ከዚህ በተጨማሪ ለምሳሌ በግብር ህግ ላይ በማተኮር ጥናትና ምርምር የሚሰሩት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ ፋኩልቲ መምህሩ አቶ ታደሰ ሌንጮ ሰኔ 3/2004 ዓ.ም ለታተመው የሪፖርተር ጋዜጣ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ገፅ 15 ላይ "በአንድ በኩል በእኛ ሀገር ዜጎች ታክስ እና ግብር የመክፈል ባህል የላቸውም" የሚል ድምዳሜያቸው ተጠቅሷል::

በተቃራኒው ደግሞ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ግብር በፍትሐብሔር መጠየቅ እየቻለ ግብር ከፋዩን በትናንሽ ጥፋቶች ሣይቀር በወንጀል ተጠያቂ ማድረጉ ለግብር ከፋዩም፣ ለመንግስትም፣ለሐገር እድገትም የሚበጅ አይደለም በሚል የሚከራከሩ አሉ::[16]

በሐገራችን በግብር ከፋዩ በኩል ያለው ቅሬታ ለምን የወንጀል ሐላፊነት ወይም የገንዘብ ቅጣት ኖረ ሣይሆን የቅጣት መጠኑ በጣም ከፍተኛ እና ከሚፈፀመው ስህተት *ወይም ጥፋት ጋር ሲነፃፀር* ተመጣጣኝ ያልሆነ፤ አንዳንድ ጊዜም የቅጣቱ መጠን ድርጅቱን እስከመዝጋት የሚያደርስ ስለሆነ ቅጣቱ ከባድ ነው፣ ግብር ከፋዩ በቅን ልቦና የሠራውን ስህተትም ለማረምና ለማስተማር የሚደረገው ጥረት አነስተኛ ነው የሚል ቅሬታ በግብር ከፋዩ በኩል እንዳለ ጥናቶች ይጠቁማሉ::[17]

በግብር ሰብሣቢውም በኩል የወንጀል እርምጃ የመጨረሻው የማስተማሪያና የመቅጫ እርምጃ እንጂ እንደመደበኛ እርምጃ እየተወሰደ ያለ አይደለም በሚል የሚቀርብ መከራከሪያ አለ::[18] በርግጥም የታክስ ሕጎቹን የወንጀል ድንጋጌዎች ብዛት ልብ ብሎ ለተመለከተ ሰው በግብር ከፋዩ በኩል እየተፈፀመ ያለው ስህተት /የአውቆ ማጥፋትና የቅን ልቦና ስህተት/ ሁሉ የወንጀል ክስ ይመስረትበት ቢባል ማንም ከተጠያቂነት ይድናል ብሎ መገመት አይቻልም:: ባለስልጣን መ/ቤቱ ይህን መከራከሪያ የሚያቀርበው ከዚህ አንፃር በመመልከትና "በእያንዳንዱ የታክስ ጥፋት ላይ *የወንጀል* ክስ ልመስርት ብል በርካታ ግብር ከፋይ ሊከሰስና ሊቀጣ ይችል ነበር"፣ ይሁን እንጂ የወንጀል ክስ እየመሰረተን ያለነው በጥቂት ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው በሚል አስተሳሰብ ይመስላል:: በአጠቃላይ ግን በታክስ ጉዳይ የወንጀል ክስ የመጨረሻ አማራጭ፣ በአውቆ ማጥፋት ላይ የሚመሠረት፣ የግብር ከፋዩን የአካልና የሥራ ነፃነት የማያሳጣ፣ የድርጅቱን ህልውና ክፉኛ የማይጐዳ መሆን አለበት የሚለው አስተሳሰብ በመስኩ ባለሙያዎችና በግብር *ፖሲሲ* አውጪዎች በኩል መግባባት ላይ የተደረሰበት መሠረታዊ ሐሣብ ነው::

## 2.2 የታክስ ወንጀል ሕጐቻችን

የታክስ ወንጀል በወንጀል አይነት አመዳደቡ በአብዛኛው በመንግስት የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ የሚፈፀም ወንጀል ተደርጐ የሚመደብ ነው::በወንጀል ሕጉ ላይም የተመደበው በዚህ አመዳደብ ነው::[19] የግብር ወንጀል መሠረት የሚያደርገው በወንጀል ሕጉ ላይ ከተደነገጉት ወንጀሎች በተጨማሪ[20] በተለያዩ የግብር አዋጆችና ደንቦች ላይ የተደነገጉትን የወንጀል ሐላፊነት የሚያስከትሉ ድንጋጌዎችን ጭምር ነው:: የገቢ ግብር አዋጁ፣የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ፣የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በርካታ የወንጀል ድንጋጌዎችን ይዘዋል::እነዚህ ድንጋጌዎች በጠቅላላ የታክስ ወንጀሎች በሚል ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው:: የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን ብቻ ስንመለከት አዋጁ የወንጀል ድንጋጌዎቹን "የወንጀል ጥፋቶች" በሚል ርዕስ በክፍል 12 ላይ ዘርዝሯቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት ይህ ክፍል ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር

---

16 ይህ አስተሣሰብ የገንዘብ ቅጣትንም ይጨምራል:: በወንጀል እንዲከሰሱ ሳይደረግ ከፍተኛ ገንዘብ መቅጣትም የባለሐብቶች ወይም የባለአክስዮኖች ገቢ ወይም የትርፍ ድርሻ እንዲቀንስ ስለሚያደርግ፣ ለሠራተኞች የሚሰጡ የተለያዩ ጥቅማጥቅሞች እንዲቀንሱ ስለሚያደርግ፣የሠራተኛ ቅነሣም ሊያስከትል ስለሚችል ጥንቃቄ የሚፈልግ እርምጃ ነው በሚል የሚከራከሩ አሉ /ለምሣሌ ጠበቃ ይሁን ፀሐይ ይህን አይነት አስተሳሰብ ካላቸው ባለሙያዎች መካከል አንዱ ነው::

17 ለምሣሌ አሚን እና ጆን ማስታወሻ ተ.ቁ. ገጽ 39

18 የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤቱ የቴሌቪዥን ፕሮግራም፣ ጋዜጣና መሰል ዘገባዎች ላይ ይህ አስተሳሰብ በተደጋጋሚና በስፋት የሚነገር ነው::

19 የ1996 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ/ ከዚህ በኋላ "የወንጀል ሕጉ"/ በሚል ብቻ ይጠቀሣል:: በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በሚል የተጠቀሰውን ክፍል ይመለከቷል::

20 ለምሣሌ የወ/ሕ/ቁ. አንቀጽ 349፣350 እና 351 ይመለከቷል::

በተያያዘ ምን አይነት ተግባራት እንደሚያስቀጡ፣ እነማን እንደሚቀጡና የወንጀል ተሣትፎ አይነትንና ያስቀጥተኛ የወንጀል ተሣትፎ ሲቀጡ የሚችሉ እነማን እንደሆኑ በዝርዝር ደንግጓል። ይህን ወንጀል መተላለፍ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን እንደመተላለፍ የሚቆጠር ስለሆነ ክርክሩ የሚመራው በወንጀለኛ መቅጫ ስነስርአት ሕጉ /ከዚህ በኋላ "የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ" በሚል ይጠቀሣል/መሠረት ነው።[21]

የዚህ አዋጅ ማሻሻያ የሆነውና የዚሁ አዋጅ አካል እንደሆነ የሚቆጠረው አዋጅ ቁጥር 609/2001 ተጨማሪ የወንጀል ድንጋጌዎችን ይዟል። በዚህ መሠረት ማሻሻያው ደረሰኝ ከመስጠት ግዴታ ጋርና ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ምን አይነት ተግባር በወንጀል እንደሚያስጠይቅና እነማን ሊጠየቁ እንደሚችሉ ደንግጓል። በዚህ መሠረትም ማንኛውም ለተ.እ.ታ. የተመዘገበ ግብር ከፋይ ከግብይቱ በኋላ ወዲያውኑ ደረሰኝ ካልሰጠ በወንጀል እንደሚጠየቅ ደንግጓል።

ይህ ግዴታ የተጣለው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በሚጠቀሙና በማይጠቀሙ ተመዝጋቢዎች ላይ ነው።ይህን ግዴታቸውን ካልተወጡ በወንጀል ይጠየቃሉ።[22] በዚህ መሠረት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ /ከዚህ በኋላ "ዐ/ሕግ" በሚል ይጠቀሣል/ የወንጀል ክስ እየመሠረተ በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ተፈርዶባቸዋል። አሁንም በክርክር ላይ ያሉ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ ክሶች ይገኛሉ። በሥራ ላይ ካሉት የታክስ ሕጐች በፊት የነበሩት የተሻሩት የታክስ ሕጐችም የወንጀል ድንጋጌዎችን ይዘው የነበር ቢሆንም እንደጉምሩክ ወንጀሎች የወንጀል ክስ በብዛት የተመሠረተባቸው የነበረ ስመሆኑ አጠራጣሪ ነው።[23] በተገኘው መረጃ መሠረት ከ1996 ዓ.ም በፊት በግብርና ታክስ ጉዳይ ላይ የቀረበ የወንጀል ክስ የለም። በጉምሩክ ጉዳዮች ግን በርካታ የወንጀል ክሶችና ፍርዶች አስቀድሞ ከ1996 ዓ.ም በፊትም ነበሩ።[24]

የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ምንነት ማብራሪያ የሚፈልግ አይደለም። በመሣሪያው የታተመ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ምንነትን በተመለከተ ግን ወደ ዝርዝር ጉዳዮች

---

21 አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 48 ይመለከቷል።

22 የተጨማሪ እሴት ታክስ /ማሻሻያ/አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀጽ 50/ሰ/ እና አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 48 እና የዚህኑ ሕግ ማብራሪያ የሆነውን 'የተጨማሪ እሴት ታክስን በሥራ ላይ ለማዋል ስለተዘጋጀው አዋጅ ረቂት የቀረበ አጭር መግለጫ፣ ያልታተመ :ገጽ 42 ይመለከቷል። ይህ የማብራሪያ ሰነድ የታክስ ሕጉ ምንጭ ሰነድ (source document) ተደርጐ የሚወሰድ ነው። የወንጀል ድንጋጌዎቹን በተመለከተ ግን *የማብራሪያ ሰነዱ* ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ አይደለም።

23 በታክስ ጉዳዮች ላይ የተመሠረቱ የወንጀል ክሶች ስለመኖራቸው ፀሐፊው መረጃ ማግኘት አልቻለም። አጠራጣሪ ነው የተባለውም ፀሐፊው ሲያገኛቸው ያልቻሉ ጉዳዮች ሲኖሩ ይችላሉ በሚል እምነት ብቻ ነው። ፀሐፊው ለረዥም ጊዜ በገብር ሕጐች ላይ ከሰሩት ከሚች ከአቶ ግርማ ሐ/መስቀል ጋር ባደረገው ተደጋጋሚ ውይይት እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ የወንጀል ክስ ስለመቅረቡ እንደማያውቁ ገልፀውለታል። በታተመሙ የፍርድ ቤት ውሣኔዎች ላይም የታክስ ወንጀል ጉዳይ አላጋጠመውም።

24 የቀድሞው የጉምሩክ ባለስልጣን በጉምሩክ ወንጀሎች ላይ እራሱ ምርመራ በማድረግ በራሱ ዐ/ሕግ የወንጀል ክስ ይመሠርት ነበር። የቀድሞው ገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ሐገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ግን የራሱ ዐ/ሕግ አልነበረውም።*አንዳንድ ጊዜ የታክስ ወንጀል ጉዳይ ለምን በመደበኛው ዐ/ህግ አይታይም የሚል አስተይየት ይሰማል የሌሎች ሀገሮች ልምድ ሲታይም የተለየ ነው። ለምሳሌ በአውስትራሊያ የግብር ኮሚሽኑ እራሱ ክስ ይመሰርታል(ከላይ በማስታወሻ ተ.ቁጥር 11 ላይ የተጠቀሰውን ድህረ ገፅ ASKŸ...M። በስዊዘርላንድ ደግሞ በዐ/ህግ መ/ቤቱ ውስጥ እያንዳንዱ መምሪያ የተዋቀረው የገቢዎች እና ጉምሩክ የስራ ክፍል ክስ ይመሰርታል።* (http:/ynamtax.co.uk/abouttax/tax prosecution.php/3/18/tax.prosecutions/

ከመግባታችን በፊት ስለመሣሪያው ምንነት የሕግ ግንዛቤ መያዝ ስለሚያስፈልግ ይህንኑ እንደሚከተለው በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

### 3. ስለሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ምንነት

በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታን የደነገገው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጉም ሰጥቶታል፡፡ በዚህ መሠረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ (cash register machine) ወይም የሽያጭ **ነቁጥ** መሣሪያ (Point of Sales Machine) ነው በማለት ደንቡ ተርጉሞታል ፡፡ የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ እና የሽያጭ ነቁጥ መሣሪያ ማለት ምን ማለት እንደሆነም ትርጉም ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በሽያጭ መደበኛ ደረሰኝ ምትክ የሸቀጦችን ወይም አገልግሎቶችን ሽያጭ የሚመዘግብና ስማንበብ ብቻ የሚቻል ማስታወሻን የሚያከማች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ፕሮግራም የሚደረግ ቲን የተገጠመበት በሰርኪዩት የተረጋገጠ ፕሮግራም የሚጠቀም፣ ወይም ተጨማሪ ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ተጨማሪ አቅም ያለው መሣሪያ ነው፡፡[25]

ይህ መሣሪያ ነጋዴዎች በተለመደው ሁኔታ ሲጠቀሙበት ከነበረው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ (Cash register Machine) መሣሪያ[26] ይለያል፡፡ የሚለይበት *መሰረታዊ* ምክንያትም የታክስ አከፋፈልን በተመለከተ አስፈላጊ መረጃ የሚሰውና ከማዕከላዊ የመረጃ ማዕከሉም ጋር ያልተገናኘ በመሆኑ ነው፡፡ የመሣሪያውን ደዘትና አቀራረብ በተመለከተ መሣሪያው ሕጋዊ እውቅና እንዳለው የሚቆጠረው በአቅራቢነት ከተመዘገቡ አቅራቢዎች የተገዛና የተገጠመ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ በቴክኒካል መሣሪያነታቸው እነዚህ መሣሪያዎች እንደሚጫንላቸው ሶፍትዌር አይነት፣ ከሒሣብ አያያዝና የክምችት አስተዳደርን (Stock management) ለመቆጣጠርና ለግብር መረጃ አቀባበል ካላቸው የቴክኒዩሎጂ ብቃት አንፃር የተለያዩ ደረጃና ጥራት አላቸው፡፡ በዚህ መሠረትም ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን መስፈርት አሟልተው በአቅራቢነት የተመዘገቡና ማሽኑን እያቀረቡ ያሉ በሕጉ አነጋገር "አቅራቢዎች" የሚባሉ ድርጅቶች አሉ፡፡ *ስለሆነም ተመዝጋቢው ግብር ከፋይ መሳሪያውን ሊገዛና ሊጠቀም የሚገባው ለእዚሁ ባአቅራቢነት ከተመዘገቡት ተቋማት ብቻ ነው፡፡ ይህን አለማድረግ የህግ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡*

### 4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ግዴታዎች

ደረሰኝ የመስጠት ግዴታታ ያለባቸዉ የተ.ኢ.ታ *ተመዝጋቢዎች* /*ከዚህ በኋላ ተመዝጋቢዎች በሚል የሚጠቀሱ*/ *በሁለት የተከፈሉ ናቸዉ፡፡* ታአንደኛው ክፍል መሣሪያውን የሚጠቀሙ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ መሣሪያውን የማይጠቀሙ በደረሰኙ ብቻ ሽያጭ የሚያከናውኑ ናቸው፡፡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ለመጠቀም ግዴታ ያለባቸው ግብር ከፋዮች እነማን እንደሆኑ የሚለየው በደንቡ መሠረት ሣይሆን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ነው፡፡[27] በዚህ መሠረትም አመታዊ ሽያጫቸው ከብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በላይ ከሆኑ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ በተለያየ ጊዜ በወጡ መመሪያዎች መነሻነት በአስመጪነት፣ በላኪነት፣

---

25 ደንብ ቁጥር 139/99 አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ 1፣2 እና 6 ላይ የተደነገጉትን የትርጉም ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ይመለከቷል፡፡

26 ይህ መሣሪያ ከታክስ የመረጃ ማዕከል ጋር ግንኙነት የሌለው ነጋዴዎች የተ.እ.ታ. አዋጅ ከመውጣቱ ከ1994 ዓ.ም በፊትም ይጠቀሙበት የነበረው መሣሪያ ነው፡፡ በአብዛኛው ትላልቅ ሆቴሎች ፣ ሬስቶራንቶች ፣ መጠጥ ቤቶች የችርቻሮ መደብሮች ፣ሱፐርማርኬቶች ይጠቀሙበት ነበር፡፡

27 ከላይ በማስታወሻ ቁ. 25 ላይ የተጠቀሰውን ደንብ አንቀጽ 3 ይመለከቷል፡፡

በማምረት፣ በጅምላ ማከፋፈል፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ ወዘተ ዘርፍ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት እንዲመዘገቡ ተደርጓል::[28]

በበርካታ ሐገሮች እንደተደረገው[29] ሁሉ በአዋጁ የመሸፈን ጉዳይ የሽያጭ መጠን መሠረት ያደረገ ነው፣ በፈቃደኝነት ያልተመዘገቡት ግን በንግድ ዘርፋቸው አይነት፣ በንግድ ቦታቸው ወዘተ ምክንያት የግዴታ ተመዝጋቢ እንዲሆኑ ተደርገዋል::አሁንም በዚህ መልክ እየተሰራ ይገኛል:: አመታዊ ሽያጫቸው ብር 500,00.00 የማይሞላ ግብር ከፋዮች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት መመዝገብ ይችላሉ:: አብዛኛው ገዢያቸው/ግብአታቸው/ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች ጋር የሆኑ ነጋዴዎች የከፈሉትን ተ.እ.ታ. ለማስመለስ ወይም ለማወራረድ የሚያስችላቸው እራሳቸውም ተመዝጋቢ ከሆኑ ስለሆነ የተጠቀሰው የሽያጭ መጠን ሣይኖራቸው የተመዘገቡ አሉ::

ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ ግብር ከፋይ ደረሰኝ ሲሰጥ የሚገባውና መሣሪያውን ሲጠቀም የሚገባው በዘፈቀደ ሣይሆን በሕግ የተቀመጡ ግዴታዎችን አክብሮ በመከተል ነው:: በዚህ መሠረት የተመዘገቡ ግብር ከፋዮች በመሠረታዊነት የሚከተሉት ሁለት ግዴታዎች አሉባቸው:: እነዚህም፤

1. ደረሰኝ ወዲያውኑ የመስጠትና[30]
2. በእያንዳንዱ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ሒሣቡን ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ማሣወቅ[31] ናቸው::

ከዚህ በተጨማሪ ከሽያጭ መሣሪያ አጠቃቀም ጋር በተያያዘም ግብር ከፋዩ በባለስልጣን መ/ቤቱ ከተፈቀደው ውጪ እንዳይጠቀም፣ጥገና እንዳያስደርግ፣በአመት አንድ ጊዜ የቴክኒክ ምርመራ እንዲያስደርግ ወዘተ ግዴታ አለበት:: ተጠቃሚዎች እነዚህን ግዴታዎች ካልተወጡ ሊከተልባቸው የሚችል የወንጀልና የፍትሐብሔር ሐላፊነቶች በሕጉ ላይ ተደንግገዋል::[32] የፍትሐብሔር ኃላፊነቱ የዚህ ጽሑፍ መሠረታዊ ትኩረት ስላልሆነ የምንመለከተው አይደለም::የወንጀል ኃላፊነትን በተለይም ደረሰኝ ወዲያውኑ አለመስጠትን በተመለከተ ያለውን የወንጀል ሐላፊነት ግን ቀጥሎ እንመለከታለን::

## 4.1 ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ

ተመዝጋቢዎች ዕቃ ወይም አገልግሎት ለገዛው ሰው ደረሰኝ መስጠት ግዴታ አለባቸው:: ይህን ግዴታ የሚጥለው አዋጅ ቁጥር 285/94 ያሻሻለው አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 10/1/"... ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበና ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያካሒድ ሰው ደረሰኝ ወዲያውኑ መስጠት አለበት" በማለት ይደነግጋል:: ይህ ድንጋጌ ከእንግሊዝኛው ትርጉም ጋር መጠነኛ ልዩነት ያለው ይመስላል::ወዲያውኑ የሚለውን የአማርኛ ቃል " to simeltanously issue" በሚል ተተርጉሟል:: የእንግሊዝኛው ትርጉም "አብሮ መስጠት "የሚለውን የአማርኛ ትርጉም የሚመለከት ነው:: በመሆኑም በአማርኛው ድንጋጌ መሠረት ለገዢው ደረሰኝ ሲሰጥ የሚገባው ገንዘቡን እንደከፈለ ወዲያውኑ መሆን አለበት የሚል ሲሆን በእንግሊዝኛው ደግሞ ገንዘቡ የሚከፈለው ደረሰኝ ከመቀበል ጋር መሆን አለበት እንደማለት ነው::

---

[28] ለምሣሌ ጥር 28 ቀን 2002 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የወጣውን የህዝብ ማስታወቂያ ይመለከቷልለምሣሌ በእንግሊዝ ሐገር አመታዊ ሽያጫቸው ከ70,000.00 ፓውንድ በላይ የሆኑ ነጋዴዎች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ አለባቸው (ACCA paper F6 Taxation(UK) FA 2010 AND F(NO.2) A2010 study Text for exams in 2011 pp 326

[29] አ.ቁ. 609 አንቀጽ 10/1/ ይመለከቷል::

[30] አ.ቁ. 609 አንቀጽ 12/1/ሀ/ ይመለከቷል::

[31] አ.ቁ 609/2001 አንቀፅ 10/1 እና 12/1/ሀ ይመለከቷል::

[32] የአዋጁን አንቀጽ 18/47/ሀ/ ይመለከቷል::

በሴላ በኩል ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ተከናወነ የሚባለው ለግብይቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሲሰጥ ነው በማለት አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 11/1/ ይደነግጋል:: ይሁን እንጂ ደረሰኝ ሲሰጥ የሚችልበት ጊዜ አቅርቦቱ ከተከናወነ በኋላ እስከ አምስት ቀናት ውስጥ ሲደርስ እንደሚችልም የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ይደነግጋሉ:: የንግድ አሰራርና የሽማቾች ጥበቃ አዋጅም ነጋዴው ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት የሚል ሲሆን ነጋዴው ደረሰኝ ሲሰጥ የሚገባበትን[33] የጊዜ ሁኔታ ግን አላመለከተም::

ይህ አዋጅ የሚመለከተው ማንኛውንም ነጋዴ ሲሆን ለተ.እ.ታ. የተመዘገቡ ነጋዴዎችም በዚህ ግዴታ ውስጥ እንደሚካተቱ ግልጽ ነው:: እነዚህን ድንጋጌዎች በጥንቃቄ ስንመለከት ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች ይነሣሉ፣ አንደኛው ተመዝጋቢው ግዴታውን እንዳልተወጣ የሚቆጠረው ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ ምን ያክል ጊዜ ቀይቶ ደረሰኝ ካልሰጠ ነው የሚለውና፣ ገዥው ደረሰኝ እንዲሰጠው መጠየቅ የለበትም ወይ? የሚሉት ናቸው:: እነዚህን *ጥያቄዎች* በክርክር *ጊዜ ከሚያጋጥሙ የክርክር ነጥቦች* አንፃር እንደሚከተለው እንመለከታለን:: ከበርካታ ክርክሮች እንደሚታየው የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተቆጣጣሪዎች ወደነጋዴው ይሄዱና አገልግሎት ወይም ዕቃ ይገዛሉ:: ለገዙት ዕቃ ወይም አገልግሎት ገንዘብ ከከፈሉ በኋላ ደረሰኝ እንዲሰጣቸው የተወሰነ ጊዜ ይጠብቃሉ፣ወይም ወጣ ይሉና ትንሽ ቆይተው ተመልሰው ይገባሉ::

ነጋዴው ደረሰኝ እንዲሰጣቸው በፍጹም አይጠይቁም::ከዚያም ድርጅቱ የመሣሪያው ተጠቃሚ ከሆነ መሣሪያው እንዳይሠራ ያስቆሙና ጆርናል ከኮምፒዩተሩ ያወጣሉ:: በጆርናሉ ላይ የተሸጠው ሽያጭ ስለመመዝገቡ ያረጋግጣሉ::[34]

ድርጅቱ መሣሪያውን የማይጠቀም ከሆነ ሽያጭ የሚደረግበትን ደረሰኝ ይወስዳሉ::በዚህ ሁኔታ ማሽኑን ሲያስቆሙና አስፈላጊ ሰነዶችን ሲወስዱ አብረዋቸው የባለስልጣኑ መርማሪዎች ስለሚኖሩ ሽያጩን ያከናወኑትንና የድርጅቱ ባለቤት ካለ ባለቤቱን፣ የሽርክና ማኀበር ከሆነ ደግሞ ሥራ አስኪያጁን ጨምረው ምርመራ እንዲጣራባቸው ይወስዳሉ::[35] የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ምርመራውን በራሱ መርማሪዎች ለማከናወን ስልጣን ስላለው ምርመራውን የሚያደርገው እራሱ ነው::[36]

ይህ ሒደት በራሱ ተገቢ አይደለም በሚል የሚከራከሩ ባለሙያዎች አሉ:: ምክንያቱም ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል፣ተፈጽሞም ከተገኘ ገለልተኛ ሆኖ ማጣራት *ይገባዋል እንጂ የራሱን ሰራተኞች* ልኮ ሆነ ብለው ደረሰኝ እንዲሰጣቸው ሳይጠይቁና ነጋዴው *ወይም ግብር ከፋዩ ወይም ሰራተኛው* ደረሰኝ *አልሰጥም ማለቱ* ሳይረጋገጥ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታውን አልተወጣም በማለት ወደ ክስ መሄድ ተገቢ አይደለም፣ ይልቁንም ግብይቱ እንደተጠናቀቀ ሲቆጠር የሚገባው ነጋዴው ደረሰኝ እንዲሰጥ ተጠይቆ ለመስጠት እንዳልቻለ ወይም እንዳልፈለገ ሲረጋገጥ ነው የሚል መከራከሪያ

---

[33] አዋጅ ቁ. 685/2002 አንቀጽ 25 ይመለከቷል::

[34] ጆርናል ማለት እያንዳንዱ ሽያጭ፣ ዋጋና ሽያጩ የተደረገበት ሰአት የሚመዘገብበትን መረጃ የያዘ ሕትመት (print out) ነው:: የሽያጭ ማጠቃለያው ዜድ ሪፖርት (Z.report) የሚባል ሲሆን፣ ይህ ሪፖርት እንደ ጆርናሉ ዝርዝር መረጃን የያዘ አይደለም::ዐ/ህግ *በምስክርነት የሚያቀርባቸው ምስክሮች ይህን ሂደት ሲያስረዱ መስማት የተለመደ ነው ለማለት ይቻላል::*

[35] ፀሐፊው ይህን ሒደት የተገነዘበው የገቢዎችና ጉምሩክ ዐ/ሕግ ምስክሮች በጉዳዩ ላይ ምስክርነት ሲሰጡ ከሚናገሩትና በማስታወሻነት ከመዘገበው እንጂ እራሱ ሒደቱን ስለተመለከተ ወይም በሆነ አጋጣሚ ተሣትፎ ስለነበረው አይደለም::

[36] የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 587/2000

የሚያቀርቡ ጠበቆች አሉ::[37] ይሁን እንጂ በዐ/ሕግ በኩል ያለው አስተሣሰብ ደረሰኝ ስመስጠት ግዴታው የተጣለው በተመዝጋቢው ላይ ብቻ ስለሆነ ይህንን ግዴታውን አስቦና ተጠንቅቆ መፈፀም ያለበት እራሱ ተመዝጋቢው ነው:: በባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል የሚደረገው በክትትል መልክ የመያዝ ስነስርዓትንም በተመለከተ ይህን *ከመድረግ የሚከለክለው* ሕግ ካለመኖሩ በተጨማሪ በዚህ መልክ የሚያዙት ነጋዴዎች አስቀድሞ በቂ ጥናት የተደረገባቸው፣ አንዳንዶቹም በቂ ማስጠንቀቂያ፣ ትምህርትና ቅስቀሣ የተደረገላቸው ሆነው ሳለ ጥፋት ከመፈፀም *ሊቆጠቡ አለመቻላቸው የተረጋገጠባቸው* ስለሆኑ ያለው የመጨረሻ አማራጭ በዚህ መልክ ይዞ ማስቀጣት ስለሆነ ነው የሚል *መከራከሪያ ይቀርባል*::

"ወዲያውኑ" የሚለውን የጊዜ ሁኔታን በተመለከተ አከራካሪ የጊዜ መመዘኛ ይታያል:: በተለይ ከታክስ አዋጁ በኋላ የወጣው የሽማቾች መብት ጥበቃ አዋጅ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታን ብቻ እንጂ "ወዲያውኑ" በሚል የተቀመጠ የጊዜ ገደብ የለውም:: በዚህ መሠረት የሚነሣው የሕግ ጥያቄ የጊዜ ገደብን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ግዴታ በኋላ ላይ የወጣው ሕግ መሆን የለበትም ወይ? የሚለው ነው:: ሌላው ወዲያውኑ የሚለው ግዴታ ግልጽ የፍሬ ነገር መመዘኛ ስንት ደቂቃን የሚመለከት ነው የሚለው ነው::

## 5. የግብር ከፋዩ የወንጀል ተጠያቂነት

ደረሰኝ ከመስጠት ግዴታ ጋር በተያያዘ የወንጀል ኃላፊነት እንዲኖርባቸው እየተደረጉ ያሉት የግል ባለሐብቱና ድርጅቶች ብቻ አይደሉም:: በወንጀል እየተከሰሱ ያሉት መሥሪያውን በቀጥታ የሚያከናውኑ ወይም ደረሰኝ ከመስጠት ሥራ ጋር ተያያዥ የሆኑ የሽያጭ ሥራና የመሣሰሉትን የሚያከናውኑ እንዲሁም ሥራ አስኪያጅንና ወኪልንም ጭምር ነው:: እነዚህ ኃላፊነት ያለባቸው ወገኖች/ከዚህ በኋላ "ተጠቃሚዎች" በሚል ይጠራሉ/እንደየድርጅቱ ትልቅነትና ትንሽነት፣ እንደ ድርጅቱ የውስጥ አሰራር ባህሪ፣እንደድርጅታዊ አቋሙ ወዘተ የመሣሪያ አጠቃቀማቸውና የተጠቃሚዎች ሁኔታና በድርጊቱ ያላቸው ተሣትፎ ሊለያይ ይችላል::[38]

የድርጅቱ ባለቤት ገንዘብ ተቀባይም/ካሸርም/[39]፣ የሽያጭ ሠራተኛም ሆኖ የሚሰራበት ተጠቃሚ አለ[40]፣ ካሸር ለብቻ የሽያጭ ሠራተኛ ለብቻ ተመድቦ ዝርዝር የሥራ ሐላፊነት

---

[37] ለምሣሌ ጠበቃ ይሁን ፀሐይ በዚህ መልክ የሚደረገው ምርመራ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9 ድንጋጌን የሚቃረን ነው የሚል እምነት አለው:: አንዳንድ ባለሙያዎች ደግሞ ደረሰኝ ጠይቀው የማይሰጣቸው መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ግብይት እንደተጠናቀቀ ሊቆጠር አይገባም ይላሉ (*ስማቸው እንዲጠቀስ ስላልፈለጉ አልተጠቀሰም*)

[38] የድርጅቶች አሰራር፣ አደረጃጀትና መዋቅር እንዲሁም ድርጅታዊ ባህላቸው የተለያየና ውስብስብ ነው:: ይህ ሁኔታ በእኛ ሐገር ብቻ ሣይሆን በአደጉት አገሮችም ጭምር እንደሆነ ሙያዊ ጽሑፎች ይጠቁማሉ/ለምሣሌ Robert Heller;The complete guide to modern management ;2006 pp25-32

[39] ገንዘብ ተቀባይ ለሚለው ቃል የእንግሊዝኛው አቻ ትርጉም "ካሸር" " cashier" የሚለው ነው:: አንዳንድ የአማርኛ ቃላት በጊዜ ሒደት በእንግሊዝኛ ትርጉማቸው እየተተኩ በስፋት ጥቅም ላይ ሲውሉ መመልከት የተለመደ ነው:: ከእነዚህ ቃላት መካከል "ካሸር" የሚለው ቃል ነው:: በዚህ ሥራ ላይ ያሉ ግለሰቦች በምስክርነት ወይም የተከሣሽነት ቃላቸውን ሲሰጡ በአብዛኛው "ካሸር" ነኝ በሚል የሥራ መደባቸውን ይናገራሉ:: ዳኞችም አንዳንዶቹ ምን ማለት ነው በማለት በአማርኛ የተለመደውን "*የአማርኛውን* የሥራውን መጠሪያ እንዲነግሯቸው ሲያደርጉ" አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ዝም ብለው ያልፋታል:: እንዲተረጉም የሚፈልጉት ዳኞች የፍ/ቤቱ የሥራ ቋንቋ አማርኛ ስለሆነ በተቻለ መጠን በአማርኛ ተተርጉሞ መነገር አለበት ከሚል እምነት በመነሣት ይመስላል::

ተሰጥቶ የሚሠራበት ድርጅት አለ፣ የሽያጭ ሠራተኛና ካሽር ሁሉም ስልጠና ወስደው እንደሥራ ብዛቱ ሁሉም የሁሉንም ሥራ የሚሰራበት አሰራር ያለው ድርጅት አለ፡፡

አንዳንዱ ደግሞ የቤተሰብ ድርጅት ይሆንና የቤተሰብ አባላት ያለደመወዝ ወይም ያለቅጥር ግንኙነት የሚሠራበት አለ፡፡[41] አንዳንዱ ደግሞ መሣሪያውን በመኖሪያ ቤቱ አድርጐ ባለቤቱ ወይም ልጁ ብቻ የሚጠቀምበት አለ፡፡ለምሣሌ ቢሮ የሌላቸው ተቋራጮችና አማካሪዎች በዚህ ምድብ ሊካተቱ

የሚችሉ ናቸው፡፡[42] ስልጠና በመውሰድም ረገድ ያለው ልዩነት የተለያየ ነው፡፡መሣሪያውን በሚሸጠው ድርጅት ስልጠና ወስደው መሥሪያውን የሚጠቀሙ ያሉ ሲሆን ያለምንም ስልጠና መሣሪያውን የሚጠቀሙም አሉ፡፡[43] በአጠቃላይ የተለያዩ ድርጅቶች ላይ የተለያየ የድርጅት ባህሪ (organizational behaviour) ይታያል፡፡

የድርጅቱ ባህሪ አይነትና ስልጠና በመውሰድና ባለመውሰድ ረገድ ያለው የተጠቃሚው ግንዛቤ የተለያየ መሆን ለግብር ወንጀል የሚኖረውን ተጋላጭነት በመወሰን ረገድ የራሱ አስተዋጽኦ ቢኖረውም ምርጥ ተመክሮዎችን (Best Practices) በዳሰሳ መልክ በማጥናት፣ይህኛው ይሻላል የሚል መደምደሚያ ገን አያጋጥምም፡፡በአጠቃላይ ግን ደረሰኝ ወዲያውኑ ከመስጠት ግዴታ ጋር በተያያዘ ሕጉ በድርጊት ተሣትፎአቸውና ያስጥፋት ተጠያቂ ሲሆኑ የሚችሉ ሰዎችን የወንጀል ሐላፊነት መሠረት ስላስቀመጠ በዚሁ መሠረት እነዚህ ግለሰቦችና ድርጅቶች በወንጀል እየተጠየቁበት ያለውን ጥቅል የሕግና የፍሬ ነገር መሠረት ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ በእነዚህ ግለሰቦች ላይ እየቀረቡ ያሉ ክሶች ይዘትን በተመለከተ ደግሞ በሌላኛው ክፍል እንመለከታለን፡፡

## 5.1 የሠራተኞች ተጠያቂነት

ሠራተኛ ማለት ለአንድ የግል ድርጅት (Sole proprietor) ወይም ሕጋዊ ሰውነት ላለው ተቋም በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ ደመወዝ እየተከፈለው የሚሠራ ሠራተኛን የሚመለከት ነው፡፡[44] በተግባር እንደሚታየው እነዚህ ሠራተኞች በጽሑፍ የቅጥር ውል ያላቸው፣የጽሑፍ የቅጥር ውል የሌላቸው ወይም የቅጥር ደብዳቤ ያላቸው፣ወይም እነዚህ ሰነዶች የሌላቸው ሆነው፣ የደመወዝ መክፈያ ሰነድ (Payroll) ያላቸው ወይም ይህም የሌላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ሁኔታዎች በተመለከተ ድርጅቶች ያላቸው፣ አሰራርና ድርጅታዊ ባህል በጣም የተለያየ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የሚነሣ መሠረታዊ ክርክር አያጋጥምም፡፡[45]

በአጠቃላይ ለዚህ ጽሑፍ አመቺነት ሲባል ሠራተኛ ማለት ደመወዝ እየተከፈለው ለአንድ ድርጅት በገንዘብ ያዥነት፣በሽያጭ ሠራተኛነት ወይም በተመሣሣይ ሥራ ለጥቅም የሚሠራ

---

*የፌደራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.25/88 የፍርድ ቤቱ የስራ ቋንቋ አማርኛ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡*

40 ለምሣሌ ትናንሽ የመጠጥ ግሮሰሪዎች፣ባርና ሬስቶራንቶች፣ ሚኒ ሱፐርማርኬቶች

41 ለምሣሌ መርካቶ በርካታ በዚህ መልክ የሚተዳደሩ *የንግድ መደብሮች* አሉ፡፡

42 ለምሣሌ አንድ ኮንትራክተር በዚህ መልክ የሚጠቀም እንዳለ ፀሐፊው ያውቃል፡፡

43 በተለይ የመጀመሪያው ካሽር ከለቀቀ በኋላ አዲስ ካሽር ሲተካ ስልጠና ያልወሰዱትን ማሰራት የተለመደ እንደሆነ ይታያል፡፡

44 በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 ለሥራ ውል የተሰጠውን ትርጉም ይመለከቷል፡፡ ጠቅላላ በግል ባለሐብቶች እንዲሁም ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ተቋማት ከሠራተኞቻቸው ጋር ያላቸው የቅጥር ግንኙነት የሚገዛው በዚህ ሕግ መሠረት ነው፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅም ማሻሻያዎቹ ሠራተኛ ለሚለው ቃል ያስቀመጡት የትርጉም ድንጋጌ የለም፡፡

45 ፀሐፊው ይህን የተገነዘበው በሥራው አጋጣሚ ሲያውቃቸው ከቻለው የቅጥር ግንኙነቶች በመነሣት ነው፡

ማለት እንደሆነ ተደርጐ ሊወሰድ ይገባል:: የሠራተኛን የወንጀል ኃላፊነት በተመለከተ የግል ድርጅት ሠራተኛም ሆነ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ሠራተኛ የወንጀል ኃላፊነቱ ተመሣሣይ ነው:: ሠራተኞች የሚጠየቁት እራሣቸው በተሣተፉበት ተግባር ስለሆነ በአብዛኛው የሚከሰሱት እራሣቸው በቀጥታ እንደፈፀሙ ተደርጐ በሚቆጠረው ተግባር ነው:: የድርጊት ተሣትፎአቸው ሲገለጽ ግን የተለያየ ሁኔታ ያጋጥማል::

በአብዛኛው እንደሚታየው ግብይት እንዲያከናውኑና ደረሰኝ እንዲሰጡ የሚመደቡት የግብር ከፋዩ ድርጅት ተቀጣሪ ሠራተኞች ሲሆኑ እንደየ ሥራ ባህሪያቸው ተደራራቢ ሥራ የሚሠሩ፣ ለምሣሌ የሽያጭ ሠራተኞችም ሆነው ካሽርም የሆኑ ወይም የተናጠል ሥራ ብቻ የሚሠሩ ሊሆኑ ይችላሉ፣ በአንዳንድ ደረሰኞች ላይ የካሽር ስም የሚፃፍ ሲሆን በአንዳንዶች ላይ ግን አይፃፍም:: ደንቡ የካሽር ስም በደረሰኙ ላይ መጠቀስ አለበት አይልም::

በደረሰኝ ላይ የካሽር ስም የመፃፍና ያልመፃፍ ልዩነት የሚታየው እንደሚጫነው ሶፍትዌር እና እንደድርጅቱ አሰራር ቢሆንም ከተጠያቂነት አንፃር ግን ልዩነት አያመጣም:: ምክንያቱም ለተጠያቂነት ምክንያት የሆነው ድርጊት ሲፈጠር ካሽር ካለ ካሽር ተጠያቂ ሲሆን ካሽር ከሌለ ደግሞ በወቅቱ ገንዘብ የተቀበሉ የሽያጭ ሠራተኞች ወይም አስተናጋጆች አንዳንድ ጊዜም እቃ ያቀበሉ፣ ወይም ወኪል ተጠያቂ ይሆናሉ:: በተግባር በሚደረጉ ክርክሮች የግል ባለሐብቶችን በተመለከተ በአጠቃላይ የቅጥር ግንኙነት ሕጉ በሚያዘው መሠረት የመኖሩና ያለመኖሩ ጉዳይ የክርክር ነጥብ ሆኖ አያጋጥምም:: ዐ/ሕግ በክሱ ላይ "የሽያጭ ሠራተኛ" ወይም "ገንዘብ ያዥ" ወዘተ ነው በማለት ከጠቀሰም በኋላ ይህንኑ ለማስረዳት በሚል የቅጥር ውል በማስረጃነት የሚያያዝበት ክስ አያጋጥምም::

ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች *ሠራተኞችን* በተመለከተ ግን አከራካሪ የሕግ ጉዳይ ሲነሳ *ያጋጥማል*:: የድርጅት ተጠያቂነት የሚመሠረተው በሐላፊዎቹ ወይም በሠራተኞቹ ጥፋት ሳይ ስለሆነ[46] ጥፋቱን የፈፀመው ሠራተኛ *መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ሰራተኛ ያልሆነ ግለሰብ* በሐላፊነት ሲጠየቅ አይገባውም የሚል አስተሳሰብ አለ:: ሠራተኛ ያልሆነን ሰው በመመደቡ ክስ *ሊመሠረትበትና* ጥፋተኛ ሲሆን የሚገባው በሐላፊዎቹ አማካኝነት ድርጅቱ ሲሆን ይገባል *እንጂ ሰራተኛ ያልሆነው ግለሰብ መሆን የለበትም የሚል መከራከሪያ ይቀርባል*:: የወንጀል ሕጉም ሆነ የተ.እ.ታ.ክስ አዋጅ ሠራተኛ ለሚለው ቃል የትርጉም ማዕቀፍ አለማስቀመጣቸው የሕጉቹ ክፍተት ይመስላል:: ሕጋዊ ሰውነት ያላቸውን ድርጅቶች በተመለከተ የታክስ አዋጁ ቢያንስ ከተመዝጋቢው ውጪ ግብይቱን ያከናወነ ማንኛ ውም ሰው የተመዝጋቢው ሠራተኛ እንደሆነ ይቆጠራል በሚል የትርጉም ድንጋጌ ቢያስቀምጥ የተሻለ ግልጽነት ያለው ድንጋጌ ይሆን ነበር::

## 5.2. የሌሎች ሰዎች ተጠያቂነት

በአንዳንድ የግል ባለሐብት ድርጅቶች ውስጥ ተቀጣሪ ወይም መደበኛው የአሰሪ ሠራተኛ ግንኙነት የሌላቸው *ሰዎችን የተለያየ ስራ ሲሰሩ* ማግኘት የተለመደ ነው:: ባል ወይም ሚስት፣ እህትና ወንድም፣ ወይም ጓደኛ፣ የቅርብ ዘመድ፣ በገንዘብ ያዥነት፣በሽያጭ ሠራተኝነት፣ በተቆጣጣሪነት ወዘተ የሚሠሩባቸው ድርጅቶች በርካታ ናቸው:: ስለሆነም በዚህ መሠረትም በበርካታ ክሶች ላይ በእነዚህ የቤተሰብ አባላት ላይ ክስ ይቀርባል:: ለምሣሌ በአንድ ጉዳይ በባለቤቷ ወንድም ሱቅ ውስጥ ስለነበረችና ግብይት ሲደረግ ደረሰኝ አልሰጠችም በሚል ከባለቤቷ ጋር እና ከባለቤቷ ወንድም ጋር ተጣምራ የተከሰሰች አለች::[47] ሶስቱም ተከሣሾች ቤተሰብነት እንጂ የቅጥር ግንኙነት የላቸውም:: ተከሣሾቹ በመጀመሪያ አካባቢ የነበራቸው አስተሣሰብ ግለሰቧ ተጠያቂ ልትሆን የሚገባው ተቀጣሪ ከሆነች እንጂ የቤተሰብ አባል የሆነችና ደመወዝ የማይከፈላት ስለሆነ ተጠያቂ ልትሆን አይገባም የሚል

---

46 የወ/ሕ/ቁ. 34/1/ ዝርዝር ድንጋጌ ይመለከቷል::

47 ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ. 181768 ያለውን ክርክር ይመለከቷል::

ነበር። በሌላ ጉዳይም ሱቁን ጠብቂ የተባለች ሞግዚት በአጋጣሚ አልፎ አልፎ ወደሱቅ ስትመጣ ሲሸጥ የምታውቀውን እቃ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተቆጣጣሪዎች እንደገዙ ሆነው በመቅረብ እንድትሸጥላቸው ሲጨቀጭቋት ስለሸጠች ተከሣለች።[48]

ይሁን እንጂ በዐ/ሕግ በኩል ያለው የመከራከሪያ ምክንያት ደረሰኝ ከመስጠት ጋር በተያያዘ ያለው ተጠያቂነት የሚመሠረተው በወቅቱ ግብይት ሲደረግ፣ ገንዘብ ተቀብሎ ደረሰኝ ወዲያውኑ ካለመስጠት ጋር ብቻ ስለሆነ ገንዘብ ተቀብሎ ደረሰኝ ያልሰጠው ሰው ሠራተኛም ሆነ አልሆነ በኃላፊነቱ ላይ ለውጥ አያመጣም። በመደብሩ/ሱቁ/ ውስጥ ተገኝቶ ይህን ተግባር የፈፀመ ማንኛውም ሰው ተጠያቂ መሆን አለበት የሚል ነው። እስከአሁን በሚመሠረቱ ክሶች ላይም ድርጊቱን የፈፀመው ሰው ሠራተኛ ስለመሆኑና ስላለመሆኑ ይህንንም ተከትሎ ሐላፊ ሲሆን ይገባል ወይም አይገባም በሚል የሚደረግ መሠረታዊ ክርክር አያጋጥምም።

## 5.3. የግል ባለሐብቱ ተጠያቂነት

የግል ባለሐብት ማለት ከሽርክና ማኅበራት ወይም ይህን መሰል አደረጃጀት ካላቸውና የህግ ሰውነት ከተሰጣቸው ድርጅቶች ውጪ በአንድ ግለሰብ ባለቤትነት ተመዝግቦ ያለን የንግድ ድርጅት የሚመለከት ነው፡ በሐገራችን ይህ አይነት የንግድ ባለቤትነት ከፍተኛ ውን ቁጥር የሚይዝ ነው። እነዚህ ባለሐብቶችም ደረሰኝ ወዲያውኑ የመስጠት ግዴታ አለባቸው እየተባለ በዐ/ሕግ ክስ እየተመሰረተባቸው ይገኛል። በተግባር በሚታዩ ክርክሮች፣ አንዳንዶቹ ባለሐብቶች ግብይቱ ሲደረግ በቦታው ያልነበሩ ሲሆን ይኸው ፍሬ ነገርም በዐ/ሕግ ምስክሮች ሣይቀር የሚረጋገጥበት አጋጣሚ በርካታ ነው። የዐ/ህግ ምስክሮች የምስክርነት ቃላቸውን ሲሰጡ ባለሐብቱ በቦታው ነበር ወይ? ተብለው ሲጠየቁ አልነበረም ይላሉ።[49] በግብይቱ ወቅት ያልነበሩ ባለሐብቶችን በተመለከተ ሲከሰሱም ሆነ ጥፋተኛ ሲባሉ የሚገባቸው የወንጀል ተሣትፎ ካላቸው ብቻ እንጂ ያለ ወንጀል ተሣትፎ ኃላፊ ሲሆኑ የሚችሉበት የሕግ መሠረት የለም በሚል ክርክሮች ሲቀርቡ መሰማት፣ ተከሣሾች የመፋረጃ ሐሣብ ሲያቃርቡም ይህን መከራከሪያ ማንሣት የተለመደ ነው ለማለት ይቻላል።

## 5.4 የወኪል ተጠያቂነት

ወኪል ማለት በሌላ ሰው ስም እና ትእዛዝ የሚሠራ ማናቸውም ሰው ማለት ነው በሚል የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ የትርጉም ድንጋጌ አስቀምጦለታል።[50] በፍትሐብሔር ግንኙነቱ የውክልና ወካዩ ሕጋዊ ተግባራትን እንዲያከናውንለት ሲል ወካዩ ከተወካዩ ጋር የሚገባው የውል ግንኙነት ነው።[51] በንግድ ሥራ ውስጥ የሚገኙ የግል ባለሃብቶች ተግባሮቻቸውን ሌላ ሰው እንዲያከናውንላቸው ሲሉ የውክልና ስልጣን መስጠት በጣም የተለመደ።የውክልና ስልጣኑም ከተራ ጉዳይ ማስፈፀም አንስቶ የንግድ መደብራቸውን እስከመሸጥ፣ አስይዞ እስከመበደርና በማናቸውም ሁኔታ ለሶስተኛ ሰው እስከማስተላለፍ የሚደርስ ልዩ የውክልና ስልጣን ሊሆን ሲሆን ይችላል። አንዳንድ ባለሃብቶች ይህን የሚያደርጉት በቅን ልቦና እና በእውነት ላይ ተመስርተው ነው። ለምሣሌ አባት ወይም እናት በእርጅና ፣በህመም ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ተሯሩጦ መስራት ወይም የንግድ ስራውን በቅርበት ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር ስለማይችሉ ለልጅ፣ ወይም ለቅርብ

---

48 ከጠበቃ ጫንያለው እሸቱ የተገኘ መረጃ ነው።

49 ፀሐፊው በችሎት ተቀምጦ ምስክር ሲሰማና ይህ አይነት ክርክሮች ሲቀርቡ ሰምቷል። እራሱ በተከራከረባቸው ጉዳዮችም ባለሐብቱ በሌለበት ድርጊቱ በተፈፀመ ጉዳይ ክስ የተመሠረተባቸው ተከሣሾች አሉ/ለምሣሌ የመ/ቁ. 181768 ይመለከቷል።

50 አዋጅ.ቁ. 285/94 አንቀጽ 2/2መ/

51 የፍ/ሕ/ቁ. 2199

ዘመድ የውክልና ስልጣን በመስጠት የንግድ መደብሩን በውክልና እንዲመራና እንዲተዳደር ያደርጋል:: ወይም ደግሞ የግል ባለሃብቱ ልጅ ከሆኑ ለአባቱ[52]፣ ለወንድሙ፣ ለእናቱ የውክልና ስልጣን ሲሰጥ ይችላል:: በዚህ መልክ በወኪል የሚተዳደሩ የንግድ መደብሮችንም ማግኘት የተለመደ ነው::

አንድንድ ጊዜ ግን በወካዩና በተወካዩ መካከል ያለው ግንኙነት ውስጥ ለውስጥ የሽያጭ ግንኙነት የሚሆንበት አጋጣሚ አለ:: ከዚህ ውጪም ተወካዩ ሠራተኛ ወይም በየወሩ መጨረሻ ትርፉን እየተሳሰበ የተወሰነ መቶኛ ከባለቤቱ ጋር የሚካፈል ሲሆን ይችላል:: በዚህ መሠረት የንግድ መደብሩ" በውክልና ስልጣኑ መሠረት በእውነተኝነት የማስተዳደርን ጉዳይ በተመለከተ አንዳንድ ወኪል በርግጥም የሚያስተዳድር ሲሆን አንዳንዱ ግን የውክልና ስልጣን ማረጋገጫ ሰነዱን ከመያዝ ውጪ በውክልና ስልጣኑ መሠረት የሚሠራ አይደለም:: ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶችንም በተመለከተ ተመሣሣይ ነው:: ሥራ አስኪያጁ ሥልጣኑን በሙሉም ሆነ በከፊል ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ የኩባንያው መተዳደሪያ ደንብ ወይም መመስረቻ ጽሑፉ ከፈቀደለት በውክልና ከማስተላለፍ የሚከለክለው ሕግ የለም:: በተግባርም እንደሚታየው በዚህ መልክ በሚወከሉ ተወካዮች አማካኝነት የሚተዳደሩ ድርጅቶች በርካታ ናቸው::

የውክልናው ይዘትም ሲታይ ተመዝጋቢውን የንግድ መደብር ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር የሚል ሲሆን ሲችል፣ አንዳንዱ ደግሞ በደፈናው የድርጅቱን ጉዳይ ለማስፈፀም የሚል ይሆናል:: አሁን ባለው ሁኔታ በበርካታ ወኪሎች ላይ የወንጀል ክስ እየተመሠረተ ክርክር የሚደረግ ሲሆን ጥፋተኛ ተብለው የተፈረደባቸውም አሉ:: ወኪል ሆነው እየተከሰሱ ያሉት ግን የግል ባለሐብቶች ወኪል ናቸው:: ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ሥራ አስኪያጅ ወኪሎች የተከሰሱበት ጉዳይ አያጋጥምም:: የወኪል የወንጀል ኃላፊነትን በተመለከተ የሚነሱ የህግ መከራከሪያዎች ያጋጥማሉ:: የታክስ ሕጉ እንደድርጅት ሥራ አስኪያጅ የግል ባለሐብት ወኪል ያለ ወንጀል ተሣትፎ ተጠያቂ ሊሆን የሚችልበትን የሕግ መሠረት አላስቀመጠም:: በዚህ ምክንያት የወንጀል ተሣትፎ የሌለው ወኪል በ"ወኪልነቱ" ብቻ የወንጀል ተጠያቂነት አለበት በሚል ሊከሰስ አይገባም የሚል ክርክር በተደጋጋሚ ይቀርባል::[53] ለምሣሌ አንድ ሥጋ ቤት በስማቸው ያላቸው በእድሜ የገፉ ሴትዩ ከወኪላቸው ጋር ተከሰው ፍ/ቤት ቀርበው ክሱ ከተነበበላቸው በኋላ ክሱ የገባቸውና መቃወሚያ ያላቸው ከሆነም እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ ሲጠይቃቸው በተደጋጋሚ ሲያነሱትና በምሬት ሲናገሩ የነበረው፣ ውክልና ሰጥቼአለሁ፣እኔ ስለሥራው የማውቀው ነገር የለም፣ ወኪሉ በሰራው ጥፋት እኔ ልጠየቅ አይገባኝም የሚል ነበር:: ዳኛውም በእድሜ የገፉ መሆኑን ከግምት ውስጥ ሀማስገባት በትዕግስት ሲያስረዷቸው ሞከሩ::[54]

የወኪል የወንጀል ኃላፊነትን በተመለከተ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሕጉቹ በግልጽ የሚደነግጉት ነገር የለም:: በተግባር በሚታዩ ክርክሮች በርካታ ወኪሎች ከባለሐብቱ ጋር አብረው ሲከሰሱ ያጋጥማል:: ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ በሚያጋጥሙ ክርክሮች ወኪሉ ብቻ ሲከሰስ ባለሐብቱ አይከሰስም:: ባለሐብቱ ተከሶም ወኪሉ የማይከሰስበት አጋጣሚ አለ:: ይህ

52 ለምሣሌ አንድ ተከሣሽ በለሚ ያለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ድርጅት ለአባቷ በውክልና ሰጥታ ዩኒቨርስቲ በሙሉ ጊዜ ወይም በመደበኛ ጊዜ ተማሪነት ትምህርቷን ትከታተል ነበር፡

53 ለምሣሌ ጠበቃ ጫንያለው አሸቱ ይህንን ከወንጀል ኃላፊነት ጋር የተያያዘ ክርክር ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትና ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል::

54 ይህ ክርክር ሲደረግ ፀሐፊው በችሎት ተቀምጦ አዳምጧል::

ሁኔታ ከላይ በተመለከተው መሠረት በምርመራ ሒደት እንደተጣራው የወኪሉ የወንጀል ተሳትፎ መጠንና የውክልና ስልጣኑ ዓይነት ነው ተብሎ ይገመታል።

## 5.5 የድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነት

### 5.5.1 ጽንሰ ሐሣብ

ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነትን (corporate criminal liability) ድርጅቶቹ ወይም በድርጅቶቹ ስም በሚሰሩ ሃላፊዎች ወይም ሌሎች ሠራተኞች ከስራቸው ጋር በተያያዙ ለሚፈፅሙት ጥፋት ድርጅቶቹ በወንጀል ተጠያቂቂ የሚሆኑበት የወንጀል ኃላፊነት ፅንሰ ሃሳብ ነው። ድርጅቶች ባለረቂቅ ስብእናዎች (abstract entities) ስለሆኑ እንደተፈጥሮ ሰው ተይዘው ምርመራ ሊጣራባቸውና ጥፋተኛ ተብለው በማረሚያ ቤት ሊታሰሩ ስለማይችሉ በወንጀል ሐላፊነት ሊጠየቁ አይገባም በሚል አስተሣሰብ የወንጀል ክስ አይመሰረትባቸውም ነበር። ይሁን እንጂ በተለይ ከኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን አንስቶ ድርጅቶች በአንድ አገር የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ያላቸው ሚና ፍጹም እያደገ መምጣትና በንግድ ፣ በግብርና በኢንቨስትመንት፣በፈጠራ መብት ባለመብትነት ወዘተ ውስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባራት ከፍተኛ ሐላፊነት እያስከተሉባቸው ስለመጡ እንዲሁም ኃላፊዎቹና ሠራተኞቹ በጋራ በመመሳጠር በድርጅቱ በወንጀል ያለመከሰስ ነፃነት ሽፋን ወንጀል መፈፀም እየጨመረ ስለመጣ የወንጀል ሐላፊነታቸውን በሕግ መደንገግ አስፈልጓል።[55] በመሆኑም በበርካታ ሐገሮች የወንጀል ሕግ ውስጥ ድርጅቶች እንደተፈጥሮ ሰው ሁሉ የሕግ ውጤት ያላቸው ተግባራት በወኪሎቻቸው ወይም በባለቤቶቻቸው አማካኝነት ስለሚያከናውኑና በዚህም የተነሳ ወንጀል ሲፈጽሙ ስለሚችሉ ድርጅቱም ምንም እንኳን መታሰር ባይችልም በገንዘብ ቅጣት፣የንግድ ስራና ሌሎች ማናቸውም ፈቃዶቹን በመሰረዝና ንብረቱን በመውረስ በወንጀል እንዲቀጣ ይደረጋል። በተለይ በአደጉት ሐገሮች በዚህ የወንጀል ክፍል ላይና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የፍትሐብሔር ሐላፊነት (civil liability) ክርክሮች ውስብስብ ባህሪ እንዳላቸው ይታወቃል።[56]

ለምሣሌ በእንግሊዝ ሐገር የተበላሸ ባቡር የ9 ሰው ሕይወት አጥፍቶ የባቡር ኩባንያው በቸልተኝነት ሰው መግደል (corporate manslaughter by negligence) ወንጀል ተከሶ ነበር። ነገር ግን ኩባንያው ላይ የሐሣብ ክፍልን( *mens rea*) ለማስረዳት ስለማይቻል በጥፋት ላይ በተመሰረተ ሐላፊነት ብቻ ገንዘብ እንዲከፍል ተደርጓል። በርግጥ ድርጅቶች በሐላፊዎቻቸው ወይም በሠራተኞቻቸው አማካኝነት ሆነ ብለው ጉዳት ስለሚያደርሱ የወንጀል ሐላፊነት ሊከተልባቸው ይገባል የሚል መከራከሪያ በተደጋጋሚና በስፋት ቢቀርብም ከተወሰኑ በሕግ በግልጽ የወንጀል ኃላፊነትን ያስከትላባቸዋል በሚል ተግባራት ከተደነገጉት ተግባራት ውጪ በሁሉም ሁኔታ የወንጀል ሐላፊነት ሊኖርባቸው ይገባል የሚለው መከራከሪያ ተቀባይነት አላገኘም።[57]

በአገራችን የሕግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶችን የወንጀል ተጠያቂነት በተመለከተ የቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ግልጽ ድንጋጌ አልያዘም ነበር። በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ ግን

---

55 Cynthia lee and Angela Harris; criminal law፡ cases and materials 2005 pp1045-1167

56 ለምሣሌ Fried land Kent Roach; **Criminal Law and Procedure :Cases and Materials**; six edition; 1991 pp-583-600.

57 Micheal T Molan, Criminal Law; 2002,pp.81-83 And Dennis keenan; English Law; (12th ed) 1998 pp 535-538

ግልጽ ድንጋጌ ተቀምጧል።በዚህ መሠረት የመንግስት አስተዳደር አካላትን ሳይጨምር[58] የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በሕግ ላይ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሣሽነት ወይም በአባሪነት በወንጀል ሊቀጣ እንደሚችል የወንጀል ሕጉ ደንግጓል።[59] በሕግ ላይ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ ማለት ለምሣሌ፣በክብር ላይ የሚፈፀም ወንጀልን በተመለከተ[60] ከግብር ግዴታ ጋር፣በፕሬስ ጉዳይ፣ ተገቢ ካልሆነ የንግድ ውድድር ጋር ወዘተ በተያያዘ የድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት በግልጽ ተደንግጓል። በሙስና ወንጀልም የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ጉቦ ከሰጠ የሙስና ወንጀል □ላፊነት እንደሚኖርበትና በገንዘብ ሊቀጣ እንደሚችል በወንጀል ሕጉ ላይ ተደንግጓል።[61]

የድርጅት የወንጀል ኃላፊነት በግልጽ በተደነገገ ጉዳይ ላይ ብቻ እንዲሆን ያስፈለገበት ምክንያት ከመሠረታዊ የወንጀል ማቋቋሚያ አንዱ የሆነውን የሐሣብ ክፍል በቦርካታ ወንጀሎች ላይ በድርጅ„‹ን በተመለከተ ማቋቋም ስለማይቻል ነው። በአንዳንድ የወንጀል ዓይነቶችም የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ሊፈጽማቸው የማይችላቸው የወንጀል ተግባራት አሉ። ለምሣሌ የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ተቀጥሮ ሊሠራ ስለማይችል በስልጣን አላግባብ መገልገል ወንጀል ሊከሰስ አይችልም። ከፃታ ጥቃት ጋር በተያያዘ ወንጀልም ሊከሰስ አይችልም። በተግባር እየተደረጉ ካሉ ክርክሮች አንፃር በአጠቃላይ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶችን የወንጀል ሐላፊነት በተመለከተ ሁለት አከራካሪ ጉዳዮች በየጊዜው ያጋጥማሉ። አንዱ "ሰው" ለሚለው ቃል የሚሰጠውን ትርጉም መሠረት በማድረግ በግልጽ ድርጅቶች ሊከሰሱ ይችሉባቸዋል በሚል በህግ ከተደነገጉት ተግባራት ውጪ የድርጅቶችን የወንጀል ኃላፊነት ለማቋቋም አልፎ አልፎም የሚያጋጥመው ክስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የወንጀል ሕጉ ከመውጣቱ በፊት የድርጅቶች የወንጀል ኃላፊነት እንዳለ ሊቀጥር ይገባል ወይ የሚለው ነው። ይሁን እንጂ እነዚህን አከራካሪ ነጥቦች መመልከት ከዚህ ጽሑፍ ሽፋን (scope) ውጪ ስለሆነ አንመለከትም። ይህ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ በአጠቃላይ የወንጀል ሕጉ ለድርጅት የወንጀል ኃላፊነት መሠረት የሚያደርጋቸው የሕግ መመዘኛ ጉዳዮች ለሳሉ መመዘኛዎችን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

### 5.5.2 የድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት መሠረቶች

የወንጀል ሕጉ በመርህ ድንጋጌው ላይ "አንድ ድርጅት ወንጀል እንደአደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው ከኃላፊዎቹ ወይም ከሠራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሣሪያነት አላግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት በአነሣሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ ነው"[62] በማለት ይደነግጋል። በዚህ መሠረት አንድ ድርጅት የወንጀል ሐላፊነት እንዲኖርበት ለማድረግ የድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞቹ በሶስት ሁኔታዎች የወንጀል ተግባር በሚል በግልጽ የተደነገገውን ተግባር መፈፀምና በወንጀል ተሣትፎአቸውም በዚሁ ድንጋጌ ላይ በተጠቀሰው መሠረት የወንጀል ተሣትፎ ያላቸው መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል። ኃላፊዎቹ ወይም ሠራተኞቹ የሚፈጽሙት ተግባርም ሆነ ተብሎ

---

58 የመንግስት አስተዳደር አካላት ማለት ሙሉ በሙሉ በመንግስት በጀት የሚተዳደሩትን መ/ቤቶች ለማለት ነው። ለምሣሌ ሁሉም የሚኒስቴር መ/ቤቶችና በክልል ደረጃ ደግሞ ሁሉም ቢሮዎች የኮሚሽን መ/ቤቶች፣የባለስልጣን መ/ቤቶች፣የቀበሌ የወረዳና ሌሎች የአስተዳደር መ/ቤቶች በጠቅላላ የመንግስት የአስተዳደር አካላት ናቸው።

59 የወ/ሕ/ቁ. 34 ይመለከቷል።

60 ለምሣሌ ይህን ወንጀል ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ከፈፀመ በወንጀል እንደሚቀጣ የወ/ሕ/ቁ. 609 ይደነግጋል።

61 የወ/ሕ/ቁ. 427/5/ እና 90/3/ ይመለከቷል።

62 የወ/ሕ/ቁ. 34/1/ ይመለከቷል።

በሚፈፀም የሐሣብ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ወይም ሊመሠረት እንደሚገባውም ከሕጉ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል::[63] የድርጅትን ኃላፊነት ለማቋቋም መሠረት ተደርገው የተጠቀሱትን ሶስት የሕግ መመዘኛዎች እንደሚከተለው እንመለከታለን::

### 5.5.2.1 የድርጅቱን ጥቅም በሕገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ መፈፀም

የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የፈፀመው ጥፋት ሆን ብሎ የድርጅቱን ጥቅም በሕገወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ መሆን አለበት:: ለምሣሌ ድርጅቱ ትርፍ ሲያገኝ የሚገባው በአግባቡ ከሚያከናውነው ሽያጭ መሆን እያለበት፣ የሚሰበስበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለራሱ ለመጠቀም በማሰብ ሐሰተኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ እንዲታተም አድርጐ ቢጠቀም ይህ ሕገወጥ ጥቅምን እናደማራመድ ሊቆጠር ይችላል:: ድርጅቱ በሕገወጥ መንገድ ያስገባውን እቃ በደረሰኝ ቢሸጥ ድርጅቱ ይጎዳል በሚል እሣቤ ሃላፊዎቹ ወይም ሰራተኞቹ ያለደረሰኝ ቢሸጡም ተመሣሣይ ተግባር እንደፈፀሙ የሚቆጠር ነው:: ለምሣሌ የተ.እ.ታ ደረሰኝ መጠቀም በተጀመረባቸው የመጀመሪያ አመታት ገደማ ላይ ይህ ወንጀል ይዘወተር ነበር:: በዚህ መሠረትም ሐሰተኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ አሣትመው ሲጠቀሙ የተደረሰባቸውና ይኸው ተረጋግጦ የተፈረደባቸው ግለሰቦችም በርካታ ናቸው::ስለሆነም ሐላፊዎቹና ሠራተኞቹ ድርጅቱን በዚህ መልክ ለመጥቀም በማሰብ የሚፈፅሙት ተግባር የወንጀል ሐላፊነትን ሊያስከትልባቸው ይችላል:: በዚህ ሁኔታ የሚፈፀሙ ወንጀሎች አንዳንድ ጊዜ የሰራተኛው ተሣትፎ የሌለባቸው ሊሆኑ ይችላሉ:: ሥራ አስኪያጁ ወይም ሌሎች የድርጅቱ ሃላፊዎች በድብቅ ሃሰተኛውን ደረሰኝ አሣትመው ለሠራተኛው ሲሰጡና ሠራተኛው እንደሕጋዊ ደረሰኝ ቆጥሮ ሽያጭ ሊያከናውንባቸው ይችላል:: ይሁን እንጂ ሠራተኛው ደረሰኞቹ የተጭበረበሩ መሆኑን የሚያውቅ ከሆነ በሐላፊነት የሚጠየቅ ሲሆን ፈጽሞ ሲያውቅ ካልቻለ ግን በሐላፊነት አይጠየቅም::በተግባር እንደሚታየው ሃሰተኛ ሰነዶችን ከመገልገል ጋር በተያዘዘ የሚደረግ የወንጀል ክርክር ለመከላከል አስቸጋሪ ስለሆነ ሰራተኛው የራሱን ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደረግ ይገባዋል::

### 5.5.2.2 የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ መጣስ

የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በግልጽ የሚያውቀውን የድርጅቱን ሕጋዊ ግዴታ ከጣሰ የወንጀል ሐላፊነት ይከተልበታል:: የድርጅቱ ሕጋዊ ግዴታ በጣም ሰፊና አንዳንድ ጊዜም ውስብስብ ነው:: ሕግን አለማወቅ ይቅርታ አያሰጥም የሚባለው መርህ በራሱ በግለሰቡ ላይ ተፈፃሚ ቢሆንም ሶስተኛ ወገን የሆኑ የድርጅቶችን ሕጋዊ ግዴታ ማወቅ ግን በጠባቡ ሊተረጐምና ሊፈፀም የሚገባ ነው በሚል የሚከራከሩ አሉ:: በተለይ የታክስ ሕግ በባህሪው ሰፊና ውስብስብ ስለሆነ ባለሙያ ላልሆነ ሃላፊ ወይም ሰራተኛ ይቅርና ለባለሙያም አስቸጋሪ ስለሆነ "ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች ሊያውቁት ይገባል" የሚል አስተሳሰብ መውሰድ ተገቢ አይደለም:: ብዙ አገሮች መንግስታት ግብር ከፋዩን በወንጀል ተጠያቂ ላለማድረግ

---

[63] ከድርጅቶች የወንጀል ኃላፊነት ሕግ ጋር በተያያዘ አንድ የሕጐች ልዩነት ወይም አንድ የአስተሣሰብ ልዩነት እየሆነ ያለው ተጠያቂነቱ በሐላፊዎቹ ወይም በሠራተኞቹ የአውቆ ማጥፋት ላይ ብቻ ሊመሠረት ይገባል የሚለውና ከአውቆ ማጥፋት በተጨማሪም በቸልተኝነት የሚፈፀም ተግባርም የሐላፊነት መሠረት ሊሆን ይገባል የሚለው ነው/ የወንጀል ሕጉ ከጽንሰሐሣቡ አዲስነት አንፃር "በአውቆ ማጥፋት" ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ወደፊት እያደገ ሲመጣ ከሚችለው የኩባንያዎች ሥራ አንፃር የቸልተኝነት ተግባራትም ተመሣሣይ ውጤት ሲኖራቸው እንደሚችል ይገመታል::ለምሣሌ እራሱን የቻለ አከራካሪ ጉዳይ ቢኖረውም፣ በአዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀጽ 56/3/ ላይ ያለው የሥራ አስኪያጅ መከላከያ ከሥራ አስኪያጅ የቸልተኝነት ተግባር ጋር የተያያዘ ነው:: በአጠቃላይ ግን ከዚያ ጋር በተያያዘ ያለው የሕግ አስተሣሰብ ሰፊና ጥልቅ እንደሆነ የሕግ ስነጽሑፎች ያመለክታሉ

ተገቢውን ጥንቃቄ የሚያደርጉት ወደ ፍ/ብሄር ተጠያቂነት የሚያዘነብሉትም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

የወንጀል ሕጉ ኃላፊነትን የሚያቋቁመው በቀጥታ የድርጅቱን ግዴታ በመጣስ ሲሆን የታክስ ሕጉ ግን ኃላፊነትን የሚያቋቁመው ሥራ አስኪያጅ መሆንን ብቻ መሠረት አድርጐ ነው፡፡ ዝርዝር ሁኔታዎችን በተከታዩ ክፍሎች እንመለከታለን፡፡ስለሆነም ሠራተኞችና ኃላፊዎች ይህንን የድርጅታቸውን ግዴታ እንዳይጣስ ማድረግ ያለባቸው ሲሆን ይህን ግዴታ ከጣሱ ግን ድርጅቱ በወንጀል ይጠየቃል፡፡ የተ.እ.ታ ተመዝጋቢ የሆነ ድርጅት ካለበት በርካታ ህጋዊ ግዴታዎች መካከል አንዱ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የወጣ ደረሰኝ መስጠት ነው፡፡ ይህንን ግዴታ የሚያውቅ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ግዴታው እንዳይጣስ ተገቢውን ጥንቃቄና አስፈላጊውን ተግባር ሁሉ መፈፀም ያለበት ሲሆን ግዴታውን ጥሶ ከተገኘ ግን በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ በተግባር ከሚታዩ ክርክሮች አንዳር አብዛኛው በሠራተኞች ላይ የሚቀርበው ክስ ይህንን የድርጅቱን ግዴታ በመጣስ ያለ ተ.እ.ታ ደረሰኝ ሽያጭ አከናውነዋል የሚል ነው፡፡

### 5.5.2.3 ድርጅቱን በመሣሪያነት አላግባብ መጠቀም

ይህ በአብዛኛው ድርጅቱን ሽፋን በማድረግ ሌሎች ሕገወጥ ተግባራት መፈፀምን የሚመለከት ነው፡፡ለምሣሌ በሕጋዊ የፓሪስ ሥራ ሕገወጥ የፖለቲካ ቅስቀሣ ማድረግ፣ እንደ አይነት በህግ የተከለከለ የፖስቲካ አቋምን ወይም የሃይማኖት አስተሳሰብን ማራመድ ወዘተ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በህጋዊ ሥራ ሽፋን ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ ከሰዎች ሕገወጥ ዝውውር ጋር ወዘተ የሚሠሩ ሥራዎችን መስራት ወዘተ ናቸው፡፡ በዚህ መልክ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በተመለከተ የሚያጋጥም ክርክር የለም፡፡ በውጪ አገር ግን ሕጋዊ ስራን ሽፋን በማድረግ ሽብርተኝነት ሣይቀር የሚያስፋፉና በሌሎችም ሕገወጥ ተግባራት ላይ ተሰማርተዋል በሚል እየተጠረጠሩ እንዲፈርሱ፣ እንዲዘጉና ንብረታቸው እንዲወረስ የሚደረጉ ድርጅቶች አሉ፡፡

## 5.6 የወንጀል ተሣትፎን በተመለከተ

የወንጀል ተሣትፎ ለወንጀል ተጠያቂነት መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ የድርጅት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ አንድ ሕገወጥ ተግባር ሲፈጸም ስላየ፣ስለሰማ፣በቦታው ስለነበር ወይም ሠራተኛ ስለሆነ ብቻ የሚጠየቅ አይሆንም፡፡ ተጠያቂነት የሚከተልበት ተፈፀመ በተባለው የወንጀል ተግባር ውስጥ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሣሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ተሳትፎ ካለው ብቻ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ያለወንጀል ተሣትፎ የወንጀል ሐላፊነት ሊኖር አይገባም የሚለውን የወንጀል መርህ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የወንጀል ተሣትፎ አለ የሚባለውም ተከሣሹ በወንጀሉ አፈፃፀም የግዙፍ ተግባር፣ የሐሣብና የሕግ ሁኔዎች መተሳሰፉ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የወንጀል ተሣትፎ ዓይነቶችም በዘፈቀደ የሚተረጐሙና የምንረዳቸው ሣይሆኑ እራሣቸውን የቻሉ የሕግ ጽንሰ ሐሣቦች ናቸው፡፡

በዚህ መሠረት ዋና ወንጀል አድራጊነት ማለት ወንጀል ተብሎ የተደነገገውን ተግባር በቀጥታ መፈፀም ነው፡፡ ለምሣሌ አንድ ካሸር ደረሰኝ ሣትሰጥ ገንዘቡን ከገዢው ተቀብላ ዝም ብትል ወንጀሉን በቀጥታ እንደፈፀመች ይቆጠራል፡፡የማነሣሣት ተሣትፎ ደግሞ ሌላውን ሰው በመጐትጐት፣ ተስፋ በመስጠት፣ በገንዘብ፣ በስጦታ፣በማስፈራራት ወይም በሌላ በማናቸውም ዘዴ አንድ ወንጀል እንዲያደርግ ያግባባ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ የወንጀል ተሣትፎ ዓይነት በሌሎች ወንጀሎች ላይ በጣም የተለመደ የተሣትፎ ዓይነት ቢሆንም በዚህ ጽሑፍ በተያዘው ጉዳይ ግን የተለመደ የወንጀል ተሣትፎ ዓይነት አይደለም፡፡ የአባሪነት የወንጀል ተሣትፎ ዋና ወንጀል አድራጊው ወንጀል ከማድረጉ በፊት ሆነ ወይም በሚያደርግበት ጊዜ ወሬ

በማቀበል፣በመምከር፣ወንጀል የሚያደርግበትን ዘዴ ወይም መሣሪያ ወይም ግዙፋዊ እርዳታ በመስጠት ወይም ለወንጀሉ አፈፃፀም በሚጠቅም በማናቸውም ሌላ ዓይነት መንገድ አስቦ መርዳት ነው።[64] ይህም የወንጀል ተሣትፎ ዓይነት በሌሎች ወንጀሎች በጣም የተለመደ የተሣትፎ ዓይነት ቢሆንም በዚህ ጽሑፍ በተያዘው ጉዳይ ግን በብዛት የሚያጋጥም አይደለም።[65]

የታክስ አዋጁ ከእነዚህ የወንጀል ተሣትፎ ዓይነቶች ጋር በተያያዘ እንደጥፋት የተቆጠረውን የተሣትፎ ዓይነት ደንግጓል። በዚህ መሠረት የአዋጁ አንቀጽ 55 "ማንኛውም ሰው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲጣስ የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያነሣሣ ወይም በሚስጥር የተባበረ እንደሆነ እንደዋነኛው ጥፋተኛ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመጣስ ጥፋት ይፈጽማል" በማለት ይደነግጋል። በአብዛኛው በአስተናጋጅነት፣ በካሸሪነት፣ ወይም በሌላ ሁኔታ ያስደረሰኝ ሽያጭ አከናውነዋል በተባሉ ተከሣሾች ላይ የሚጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ ይህ ነው። ስለሆነም የወንጀል ተሣትፎን በተመለከተ ከወ/ሕጉ ጋር ሲነፃፀር አንዳንድ መሠረታዊ የሕግ ጉዳዮችን የሚያስነሱ ሲሆን እነዚህን ሁኔታዎች በተከታይ ክፍሎች ላይ እንመለከታለን።

## 5.7. የሥራ አስኪያጅ ተጠያቂነት

ደረሰኝ ከመስጠት ግዴታ ጋር በተያያዘ ሥራ አስኪያጅ ስላሰበት የተለዩ ሐላፊነት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ ድንጋጌ አስቀምጧል። በዚህ መሠረት አንድ ድርጅት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈፀመ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማናቸውም ሰው በድርጅቱ የተፈፀመውን ጥፋት እንደፈፀመ ተቆጥሮ በአዋጁ ላይ የተጣለው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆንበታል በማለት ይደነግጋል።[66] ድርጅቶች በአዋጁ መሠረት ካለባቸው ግዴታ አንዱ ደረሰኝ ወዲያውኑ የመስጠት ግዴታ ነው።[67] ለዚህ አላማም ሲባል ሥራ አስኪያጅ ማለት ማንን እንደሚመለከት የትርጉም ማዕቀፍ ተቀምጧል። በዚህ መሠረት የሽርክና ማኅበር አባል ወይም ሥራ አስኪያጅ ኩባንያን በሚመለከት የኩባንያው የሥራ መሪ፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም ሌላ ሹም የሰዎችን ህብረት በሚመለከት ደግሞ የሕብረቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም በዚሁ ኃላፊነት እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ ሥራ አስኪያጅ ተደርጐ ይወሰዳል።[68]

በወንጀል ሕጉ መሠረት የድርጅቶች የወንጀል ተጠያቂነት የሚመሠረተው በኃላፊዎቻቸው ወይም በሰራተኞቻቸው ጥፋት አማካኝነት ነው። ከታክስ አዋጁ የኃላፊነት መሠረት ጋር ሲነፃፀር ሥራ አስኪያጁ ከድርጅቱ ሃላፊዎች መካከል አንዱ ስለሆነና በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ ተቀጣሪም ሲሆን ስለሚችል በወንጀል ሕጉና በታክስ አዋጁ ላይ የተደነገገው የጥፋት ፈፃሚው ማንነት የተጣጣመ ነው። ይሁን እንጂ ጥፋቱን የፈፀመው ሌላ ሰራተኛ ወይም የድርጅቱ ሐላፊ ቢሆንም በታክስ አዋጁ መሠረት ሥራ አስኪያጁ ከመከሰስ አይድንም። አንድ ድርጅት በርካታ ኃላፊዎች ሊኖሩት ይችላል። ለምሣሌ የአክስዮን ማኅበራት የቦርድ አባላት ስለሚኖሩት ኃላፊዎች ተደርገው ይቆጠራሉ። ከዚህ በተጨማሪ የአንድ ድርጅት የሥራ

---

[64] የወ/ሕ/ቁ. 32፣36 እና 37 ይመለከቷል፣ በተጨማሪም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 57644 የሰጠውን የሕግ ትርጉም መመልከቱ ይመከራል።

[65] እነዚህ የወንጀል ተሣትፎ አይነቶች ጉዳዩን ቀለል ባለ አገላለጽ ለማስቀመጥ ሲባል የተገለጹ ናቸው እንጂ የወንደል ተሣትፎ አየነቶች እነዚህና በዚህ መልክ የሚገለጹ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም። የወንጀል ተሣትፎ ጉዳይ ሰፊና ጥልቀት ያለው የሕግና የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው። ለበለጠ ግንዛቤ በአቶ ፀሐይ ዋዳ የተፃፈው የወንጀል ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች የሚለውን መጽሐፍ ከገጽ 168-179 ያለውንና Philippe graven; an Introduction to Ethiopian penal law; pp93-108 ያለውን ማንበቡ ይመከራል።

[66] አ.ቁ. 285/94 አንቀጽ 56/1/

[67] አ.ቁ. 609/2001 አንቀጽ 10/1/

[68] አ.ቁ. 285/94 አንቀጽ 56/4/

አመራር አባላት እንደኃላፊ ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡[69] ስለሆነም ከሥራ አስኪያጁ በስተቀር ሌሎች ኃላፊዎች በተሣትፎ ላይ የተመሠረተ ተጠያቂነት ሲኖርባቸው የሥራ አስኪያጁ ተጠያቂነት ግን ያለወንጀል ተሣትፎ ነው፡፡ የወንጀል ሕጉን ብቻ መሠረት አድርገን ካየነው ሥራ አስኪያጅ ከድርጅቱ ኃላፊዎች መካከል ዋናው ሲሆን ጥፋት ካልፈፀመ በስተቀር ሥራ አስኪያጅ በመሆኑ ብቻ ሊከሰስ አይችልም፡፡ ስለሆነም የታክስ ሕጉ ከኃላፊዎች መካከል ሥራ አስኪያጅን ብቻ መነጠሉና እሱንም ያለጥፋት ኃላፊ ማድረጉ *የታክስ ሕጉ* የወንጀል ሕጉን እንደመቃረን የሚቆጠር ነው፡፡[70]

ከላይ በተመለከተው መሠረት ምንም እንኳን ሥራ አስኪያጅ ማለት ምን ዓይነት ኃላፊነት ያለበት እንደሆነ ትርጉም ቢሰጥም በተግባር በሚታዩ ክርክሮች ግን ከግል ባለሃብት የንግድ *መደብሮችና* የሕጋዊ ሰውነት አቋም ካላቸው ድርጅቶች ጋር በተያያዘ ሥራ አስኪያጅ ማለት ምን ማለት ነው የሚልና የግል ባለሐብት የንግድ *መደብሮች* ሥራ አስኪያጅ ሊኖራቸው ይችላል ወይ?የሚል አከራካሪ ጉዳይ ስለሚያስነሣ እነዚህን ሁኔታዎች እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

### 5.7.1 የግል ባለሐብት ድርጅት ሥራ አስኪያጅን በተመለከተ

አንዳንድ የግል ባለሐብቶች ክብ ማኅተም አስቀርፀውና ሥራ አስኪያጅ የሚሉትን ወይም የባለሐብቱን ስም በቲተር አስቀርፀው የሚጠቀሙ አሉ፡፡ ክብ ማኅተሙን የሚያስቀርጹት በድርጅታቸው ስም ነው፡፡ የሚጠቀሙት የድርጅት ስምም፣በንግድ ፈቃዱ ላይ ያለውን የባለሐብቱን ስም ወይም የድርጅት ስም ካስመዘገቡም የድርጅቱን ስም ነው፡፡ አንዳንዶቹ የተመዘገበ የድርጅት ስም ሣይኖራቸው በራሣቸው የሰጡትን ስም በንግድ ድርጅቱ በር ላይ በመለጠፍ፣ ማኅተምና የመፃፃፊያ ወረቀት አሣትሞ መጠቀም የተለመደ ነው፡፡[71] ቲተር ሲያስቀርጹም ሥራ አስኪያጅ ብቻ ወይም ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ ወይም ዋና ሥራ አስኪያጅ በሚል የሚያስቀርጹና ይህንኑ በተለያዩ መፃፃፊያዎች ላይ የሚጠቀሙ አሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሥራ አስኪያጅ ቀጥረው ኃላፊነቱንም ሙሉ በሙሉ በውል ወደእሱ አዙረናል በሚል እምነት ይህን የሚያደርጉ ባለሐብቶች አሉ፡፡

የድርጅቱን ሥራ በተወሰነ ደረጃና ሐላፊነት ተረክቦ ለማከናወን ሥራ አስኪያጅ በሚል ኃላፊነት መቅጠር የሕግ ክልከላ የለውም፡፡ ይልቁንም ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበትን ሠራተኛ

---

69 ሐላፊዎች *ማለት* እነማንን እንደሚመለከት አመላካች ትርጉም የለም፡፡ ይሁን እንጂ የቦርድ አባላትና በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3/2/ሐ/ መሠረት የሥራ መሪዎች ኃላፊዎች ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡ ለምሣሌ የቦርዱ አባላት ለኩባንያው ለአበዳሪዎች፣ ለሠራተኛው ወዘተ ያለባቸው ሐላፊነት ከፍተኛ ነው/ፈቃዱ ጴጥሮስ፡ የኢትዮጵያ የኩባንያ ሕግ; የካቲት 2004፣ ገጽ 151-164/*ያለውን ማንበቡ ለበለጠ ግንዛቤ ይረዳል፡፡ቢሆንም* እነዚህ የቦርዱ አባላት *ሃላፊዎች ተደርገው ሊወሰዱ ይገባል፡፤ አንዳንድ ጊዜ አማካሪ ብቻ የሆነ ባለሙያዎችም እንደሃላፊ ሊቆጠሩ ይገባል የሚል አስተሳሰብ አለ፡፡*

70 ይህ አመለካከት ካላቸው ባለሙያዎች መካከል አንዳንዶቹ የወንጀል ሕጉ የወጣው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ ከወጣ በኂላ ስለሆነ የወንጀል ሕጉ የመርህ ድንጋጌ በአስገዳጅ ሁኔታ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባዋል በማለት ይከራከራሉ፡፡ይህ ክርክር ጠበቆች በተደጋጋሚ ሲያቀርቡ ፀሐፊው በችሎት ተቀምጦ አዳምጧል፡፡

71 ድርጅቶች የንግድ ስም ሲጠቀሙ ስያሜው በሌላ ንግድ ድርጅት ያልተያዘ፣ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ከተረጋገጠ በኂላ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ድርጅቶች ይህን ሣያደርጉ የንግድ ስም ስያሜ የሚጠቀሙ አሉ፡፡ ሌላው ወገን የንግድ ስም ስያሜዬን አላግባብ ተጠቀመብኝ በሚል እስካልተቃወመ ድረስ ጠያቂ ስለማይኖር ትክክል እንደሆኑ አድርገው ያስባሉ፡፡ አንዳንድ ቀበሌዎች ግን ማስታወቂያ የተለጠፈበትን ግብር ሲያስከፍሉ ይህንንም እንደሚቀጣጠሩ ፀሐፊው ካጋጠመው ልምድ ተገንዝቧል፡፡

በዚህ የሥራ ድርሻ መቅጠር፣በአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነታቸው እንደ ሥራ መሪ ተቆጥሮ ከሌሎቹ ሠራተኞች የሚለይ የሥራ ግንኙነት እንዲኖረው ስለሚያደርግ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ የወንጀል ኃላፊነቱን በተመለከተ ግን "ሥራ አስኪያጅ" በሚል ስም ተጠራም አልተጠራም፣ሥራ አስኪያጁ ቅጥር ሥራ አስኪያጅ ሆነም አልሆነም በድርጊቱ ውስጥ ተሣትፎ ከሌለው በታክስ አዋጁ ላይ በተመለከተው መሠረት እንደሥራ አስኪያጅ ተቆጥሮ ሊከሰስ የሚችልበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ጊዜ የግል ባለሐብቶች ሲከሰሱ ሥራ አስኪያጅ ስለቀጠርኩ እኔ ልጠየቅ አይገባኝም በሚል የሚቀርቡት መከራከሪያ አለ፡፡[72] ስለሆነም የግል ባለሐብቶች የድርጅታቸውን ሥራ ካሸር፣ የሽያጭ ሠራተኛ ወዘተ በማለት ከፋፍለው እንደሚያሰሩት ሁሉ የተወሰኑ ሥራና ሐላፊነት ሥራ አስኪያጁ ስሆነ ግለሰብ መድበው ማሰራታቸው[73] በታክስ ሕጉ መሠረት ያለባቸውን ሐላፊነት ወይም ተጠያቂነት እንዳስተላለፉ አይቆጠርም፡፡ በዚህ ሁኔታ ያለው አስተሳሰብ የተሳሳተ ስለሆነ ከፍተኛ ትምህርት ሊሰጥበት የሚገባ ነው፡፡

### 5.7.2 ሕጋዊ ሰውነት ያላቸውን ድርጅቶች በተመለከተ

ከላይ ከተመለከቱት የግል ባለሐብቶች ውጪ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩና ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ታክስ ከፋዮች *የንግድ ማህበራት* ናቸው፡፡ ከንግዱ ማኅበራትም ውስጥ በአብዛኛው በአገልግሎትና እቃ መሸጥ ውስጥ ተሰማርተው የሚገኙት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበራትና የሽርክና ማኅበራት ናቸው፡፡ በንግድ ሕጉ መሠረት የንግድ ማኅበራት ስድስት አይነት ሲሆኑ ሁሉም በጽሑፍ በተዘጋጀ ውል መሠረት የሚቋቋሙ ናቸው፡፡ ከስድስቱ ውስጥ አምስቱ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ምዝገባ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የእሽሙር ማኅበርን በተመለከተ ግን ምዝገባ ስለማያስፈልገው ለሕዝብ ወይም ለሶስተኛ ወገኖች የሚታወቀው ሸሪክ አንዱ ብቻ ነው፡፡[74] እሱም የንግድ ፈቃድ በስሙ የተመዘገበው ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የወንጀል ተጠያቂነት ውጤቱ ከላይ ከተመለከተው ከግል ባለሐብት *የወንጀል ተጠያቂነት* ጋር ተመሣሣይ ነው፡፡

ሌሎቹ የንግዱ ማኅበራት ግን በመመስረቻ ጽሑፋቸውና በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ ሥራ አስኪያጅ ማን እንደሆነ በግልጽ ይጠቅሣል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሁለትና ከሁለት በላይ ሥራ አስኪያጆችም ሊሰየሙ ይችላል፡፡[75] ሥራ አስኪያጅና አንደ ወይም ከአንድ በላይ ምክትል ሥራ አስኪያጆች ሊሰየሙም ይችላል፡፡ ስለሆነም በተጠቀሱት ሰነዶች ላይ የተጠቀሰው የሥራ መሪ ተጠያቂ ይሆናል፡፡ እስከአሁን ክስ ከተመሰረተባቸው ድርጅቶች መካከል አብዛኛዎቹ

---

72 ፀሐፊው በሁለት ጉዳዮች በግል ባለሐብትነታቸው የተከሰሱ ተከሣሾች ክሱ ከተነበበላቸው በኋላ ይህን መከራከሪያ ሲያቀርቡ በችሎት ውስጥ ተቀምጦ አዳምጧል፡፡በሁለቱም ጉዳዮች ሥራ አስኪያጆቹ ከባለሐብቶቹ ጋር አልተከሰሱም፡፡

73 ይህ አይነት የሥራ ክፍፍል ወይም ምደባ (job classification) ድርጅቶች የአስተዳደር ነፃነታቸውን (Management Autonomy) የሚተገብሩበት የአስተዳደር ስርአት ነው፡፡ በአደጉት ሐገሮችም ቢሆን አንድን ድርጅት የተወሰነ አይነት የማኔጅመንት ስርአት ብቻ ተከተል ተብሎ በሕግ ሊገደድ አይችልም፡፡ ወደተጠያቂነት ሲመጣ ግን በዋነኝነት ተጠያቂነት ባለቤትነትን ተከትሎ ሊሔድ ይገባል የሚል አስተሳሰብ አለ፡፡ የታክስ ሕጉም ይህን አስተሳሰብ *መሰረት በማድረግ ሃላፊነትን ለማቋቋም ያሰበ ይመስላል*፡፡

74 የንግድ ሕጋችን ስለንግድ ማኅበሮች *የያዘውን* ጠቅላላ ድንጋጌዎች በዝርዝር መመልከቱ ይመከራል፡፡ *ለማሳሌ የንግድ ህጉን ስለንግድ ማህበሮች ጠቅላላ ድንግጌዎች* ከቁ. 210-226 *ይመለከቷል*፡፡

75 ፀሐፊው እራሱ በባለሙያነት በተሣተፈባቸው የኩባንያ ምስረታዎች ላይ ሁለት ሥራ አስኪያጅ እንዲሾም የተደረገባቸውን መመስረቻ ጽሑፎችና መተዳደሪያ ደንቦች ያስታውሣል፡፡ ከሁለት በላይ በሥራ አስኪያጅነት የተመደቡባቸው ኩባንያዎች እንዳሉም ከባልደረባዎቹ ጋር ባደረገው ውይይት ፀሐፊው ተገንዝቧል፡፡

ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበራት ናቸው። በአጠቃላይ ከሽርክና ማኅበራት ቁጥር መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው ይኸው የንግድ ማህበር ዓይነት ስለሆነ የተከሣሽነት መጠኑ ከፍተኛ ሆኖ ቢገኝ ብዙ የሚያስገርም አይደለም።

ይሁን እንጂ በሁሉም ሁኔታ በመተዳደሪያ ደንቡና በመመስረቻ ጽሑፉ ላይ ስሙ በሥራ አስኪያጅነት የተጠቀሰው ሰው ተጠያቂ ይሆናል ማለት ግን አይደለም። አንዳንድ ድርጅቶች ምንም እንኳን በዚህ መልክ የተጠቀሰ ሥራ አስኪያጅ ቢኖራቸውም ሥራውን እንደሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚያከናውን በግልጽ የሚታወቅ የማኅበሩ አባል፣ ወይም ኃላፊ ሲኖር ይችላል።[76] እንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ሥራ አስኪያጅ ሣይሆን ሌሎች ባለአክሲዮኖች ወይም የድርጅቱ ሐላፊዎች በኃላፊነት ሊጠየቁ ይችላሉ።

## 6. በዐ/ሕግ የሚቀርቡ የወንጀል ክሶች ይዘት

በዐ/ሕግ በኩል የሚቀርቡት ክሶች የግል ባለሃብትን በተመለከተ በግል ባለሃብቱ ላይ ፣ ካሸር ካለ በካሸር ላይ፣ በአስተናጋጅ ወይም በሽያጭ ሠራተኛ ላይ ሲሆን ድርጅቶችን ከሆነ ደግሞ በሥራ አስኪያጁ ላይ፣ በድርጅቱ ላይ እና ሽያጩን ባከናወኑ ሰራተኞች ላይ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በሱቁ ውስጥ ተገኝተው ግብይት በፈፀሙ ማናቸውም ግለሰቦች ላይ እንዲሁም በወኪሎች ላይ የወንጀል ክስ ይቀርባል። አንድ ክስ የተሟላ የወንጀል ክስ ለመባል ተከሣሹ የተላለፈውን የወንጀል ድንጋጌ፣የተፈፀመውን ተግባር ወይም የወንጀል ፍሬ ነገርና ተግባሩ የተፈፀመበትን የሐሣብ ሁኔታ መግለጽ ይኖርበታል። ዐ/ሕግ የሚያቀርባቸው ክሶችም እነዚህን ሁኔታዎች እንዲያሟሉ ይጠበቅባቸዋል። ክሱ እነዚህን መመዘኛዎች እንዲያሟላ የሚጠበቅበት ዐ/ሕግ ሶስቱም ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማስረዳት ስላለበት ነው። አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ሕጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገር ሲሟሉ ነው።[77] ይህን መሠረታዊ የሕግ መዘኛ መሠረት በማድረግ በተግባር በሚታዩ ክርክሮች የእነዚህን መመዘኛ ዎች በክስ ላይ መሟላት፣የክሶቹን የአቀራረብ ይዘትና የሚሰጡ ምክንያቶችን እንደሚከተለው እንመለከታለን። የሚቀርበው ክስ እንደተከሣሹ የሥራ ወይም የሐላፊነት ድርሻና የወንጀል ተሣትፎ ስለሚለያይ የመመዘኛዎቹን አገላለጽ እንደየተከሣሹ ልዩ ሁኔታ በመነጣጠል እንመለከታለን።

### 6.1 ሠራተኞችን በተመለከተ

ዐ/ሕግ በሚመሠርተው ክስ ላይ “ራተኞችና ሌሎች” በሚል ከላይ የተመለከትናቸው ግለሰቦች ላይ የሚጠቅሰው ሕግ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 55 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 50/መ/2 ነው"። አንቀጽ 55 የሚደነግገው ስለመርዳት ወይም ማበረታታት ሲሆን አንቀጽ 50/መ/ /2/ ደግሞ በሽያጭ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወን የሚያስቀጣ ስለመሆኑ ነው።የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የማይጠቀሙ ድርጅቶችን በተመለከተ ደግሞ አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀጽ 50/ለ/1/ ይጠቀሣል።

ሠራተኛው ግብይቱ ከደረሰኝ ውጪ እንዲካሄድ እንደረዳ የሚቆጠረው ዋናውን ጥፋተኛ እንደሆነ ከአንቀጽ 55 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። እዚህ ላይ የሚነሣው መሠረታዊ ጥያቄ

---

[76] ይህ አይነት የኩባንያ ሥራ አመራር በስፋት ያጋጥማል። ሥራ አስኪያጁ ስይስሙላ የተሾመባቸውና በሌላ ሰው ወይም በወኪል ብቻ የሚተዳደሩ ኩባንያዎች ፀሐፊው በሥራው አጋጣሚ በተደጋጋሚ ይመለከት ነበር። የአንዳንድ ኩባንያ ሥራ አስኪያጆችም ለረዥም አመት በሐገር ውስጥ የማይኖሩ እንደነበሩ አጋጥሞታል።

[77] የወ/ሕ/ቁ. 23/2/ እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 111 እና 112 ጣምራ ንባብን ይመለከቷል። ለዚህ አጠቃላይ መመዘኛ እንደልዩ ሁኔታ የተቀመጠው የወ/ሕ/ቁ. 34 እንደሆነ በወ/ሕ/ቁ. 23/3/ ላይ ተደንግጓል።

ዋናው ጥፋተኛ ማነው የሚለው ነው::[78] ሠራተኛ በግል ባለሐብቱ ወይም በሥራ አስኪያጁ ተቆጣጣሪነት የሚሠራ ሰው ስለሆነ፣ድርጅት በራሱ ጥፋት ሲፈጽም ስለማይችልና ጥፋት ሲፈጽም የሚችለው ሥራ አስኪያጁ ስለሆነ ዋንኛው ጥፋተኛ ተደርጐ የሚቆጠረው የሕግ ሰውነት ያለውን ድርጅት በተመለከተ ሥራ አስኪያጁ ሲሆን የግል ባለሐብትን በተመለከተ ደግሞ ባለሐብቱን ነው:: ስለሆነም በገንዘብ ያዡነት የሚሠራ፣ በአስተናጋጅነት የሚሠራና ገንዘብ ተቀብሎ ደረሰኝ እንዲሰጥ ወይም ደረሰኝ ሰጥቶ ገንዘብ እንዲቀበል ሽያጩ በተከናወነበት ወቅት ሐላፊነት ያለበት ሠራተኛ ይህንን ሐላፊነቱን ባለመወጣት የሚፈጽመው ተግባር እራሱን ችሎ "በዋና ወንጀል አድራጊነት" የተፈፀመ ተግባር እንደሆነ ተደርጐ የሚቆጠር ሣይሆን እንደመርዳት ወይም እንደመተባበር የሚቆጠር ነው:: ይሁን እንጂ ሠራተኞች እራሣቸው የፈፀሙት ተግባር ከሆነ የወንጀል ሕጉ ካስቀመጠው የወንጀል ተሣትፎ የመርህ ድንጋጌ አንፃር እንደመተባበር ሲቆጠር የሚችል አይደለም::

እንደመተባበር ሲቆጠር የሚገባው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ይህን ተግባር እንዲፈጽሙ ጠይቋቸው ፈቃደኛ ሆነው የፈፀሙት ሲሆን ወይም በማናቸውም ሁኔታ የተግባሩ መፈፀም የባለቤቱ ወይም የሥራ አስኪያጁ ፍላጐት ሆኖ፣ ይህንን ፍላጐቱን ለማስፈፀም ሲሉ ሠራተኞቹ ያለ ደረሰኝ ሸጠው ሲገኙ ነው:: በተግባር በሚታዩ ክርክሮች ግን የዐ/ሕግ ምስክሮች ቀርበው ይህን የመረዳዳት ወይም የመተባበር ፍሬ ነገር ሲያስረዱ አያጋጥምም:: በአንዳንድ ክሶች ላይ ግን ሠራተኞች በቀጥታ የሚፈጽሙትን ተግባር በዋና ወንጀል አድራጊነት እንደፈፀሙት ሆኖ የወ/ሕ/ቁ.32/1/ ተጠቅሶ የቀረቡ ክሶች አሉ:: በዚህ መልክ የቀረቡ ክሶች የወንጀል ተሣትፎውን አይነት እንደሕጉ አነጋገር በሚገባ የገለጹ ክሶች ናቸው ለማለት ይቻላል::

በሐሣብ ሁኔታ አጠቃቀስም ልዩነት ይታያል:: ለምሣሌ በአንድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ በተከሰሰበት ጉዳይ[1] ላይ 3ኛ እና 4ኛ ተከሣሾች በሆኑት ሠራተኞች ላይ የቀረበው ክስ ("... ሁለቱም ተከሣሾች በመንግስት ታክስ ላይ ጉዳት ለማድረስ ሆን ብለው ያለደረሰኝ ሽያጭ በማከናወናቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾችን በመርዳትና በመተባበር በፈፀሙት ወንጀል ተከሰዋል"[79]) የሚል ነው:: 1ኛ  ተከሣሽ ማለት ኩባንያው ሲሆን 2ኛ ተከሣሽ ደግሞ ሥራ አስኪያጁ ነው:: ሌላ ሁለተኛ ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማኅበር ሠራተኞች ላይ የቀረበ ተመሣሣይ ክስ ስንመለከት ደግሞ ("... 1ኛ ተከሣሽ የተጣለበትን ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ በታተመ ደረሰኝ ግብይት የማከናወን ግዴታ እንዳይወጣ በመተባበራቸው በፈፀሙት የመተባበር ወንጀል ተከሰዋል") የሚል ነው::[80] 1ኛ ተከሣሽ ማለት ኩባንያው ነው:: ሁለቱን ክሶች ስናነፃጽራቸው ሁለተኛው ክስ ሠራተኞቹ ተግባሩን የፈፀሙበት የሐሣብ ክፍልን ፈጽሞ አይጠቅስም:: ሠራተኞቹ ድርጊቱን የሚፈጽሙት አንድ የተወሰነ ውጤት ለማስገኘት ነው ተብሎ ይታመናል:: የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 58/1/ሀ/ ማንም ሰው አስቦ ወንጀል አደረገ የሚባለው አንድ የተወሰነ ውጤት ለማግኘት ብሎ ሲያደርገው እንደሆነ ይደነግጋል::

---

[78] በአንድ ክርክር ከኩባንያው ሥራ አስኪያጅ ጋር ተጣምረው የተከሰሱ ካሸርና አስተናጋጆች የጥፋተኝነት ቃላቸውን ሲሰጡ ባለቤቶቹ በደረሰኝ አትሽጡ ስለሚሉን ነው በማለት ቃላቸውን ሰጥተው ነበር:: ባለቤቶቹ ደግሞ ያለደረሰኝ እየሸጡ ገንዘቡን ኪሣቸው ስለሚከቱ በዚህ አንግባባም ፣ ስለሆነም ለምን አንታመንም በሚል ለማጥቃት ሲሉ ነው በዚህ መልክ ቃላቸውን የሰጡት ይላሉ:: በተለይም በቅጥር ሠራተኛ ላይ ተመስርቶ የሚደረግ ሽያጭ በደረሰኝ መሠራቱ ግብር ከፋዩን ይጠቅመዋል:: ያለደረሰኝ መሆኑ ደግሞ ይጐዳዋል:: በባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መጠቀም ለግብር ከፋዩ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ትምህርት ከሚሰጥባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ *መሳሪውን መጠቀም* ነጋዴው ሽያጩን በአግባቡ እንዲቆጣጠር ያስችለዋል የሚል ነው::

[79] ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 183174 ዐ/ሕግ ያቀረበውን ክስ ይመለከቷል::

[80] ዐ/ሕግ መጋቢት 19/2004 ዓ.ም የመሠረተውን  ክስ ይመለከቷል::

ደረሰኝ ከመስጠት ግዴታ ጋር በተያያዘ ሠራተኞች ደረሰኝ የማይሰጡት በመንግስት ታክስ ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም ኩባንያውን ለመጥቀም መሆን አለበት፡፡ የድርጅት ሠራተኞች ከሆኑ ደግሞ ድርጅቱ ደረሰኝ ለመስጠት ያለበትን ግዴታ በመጣስ የተፈፀመ ተግባር እንደሆነ ከተጠቀሰም በቂ ነው፡፡ስለሆነም ድርጊቱን የፈፀሙት ከዚህ ሐሣብና ግብ አንፃር መሆኑ በክሱ ላይ መጠቀሱ የቀረበውን ክስ የተሟላ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ረገድም የመጀመሪያው ክስ የተሟላ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ረድተዋል ወይም ተባብረዋል በሚል የሚገለፀው የወንጀል ተሣትፎ ዓይነት ግን በምን መልክ እንደተባበሩ በቂ የፍሬ ነገር ዝርዝር የሌለው ስለሆነ የወንጀል ተሣትፎ አገላለጽ መመዘኛንና ጽንሰሐሣብን የሚያሟላ አይመስልም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግል ባለሐብት ድርጅት ሠራተኛ ተከሣሽም ላይ የሐሣብ ሁኔታ አገላለጽ ተመሣሣይ ችግር ይታያል፡፡ ለምሣሌ በአንድ ክስ ላይ የተጠቀሰው" ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ በመሸጡ የግል ባለሐብቱ ያለበትን ግዴታ እንዲጥስ በመርዳት በፈፀመው ወንጀል ተከሷል" የሚል ነው፡፡ በዚህ ክስም ሠራተኛው ተግባሩን የፈፀመበት የሐሣብ ሁኔታ አልተጠቀሰም፡፡

ይህ ችግር የመነጨው የታክስ ሕጉ ከወንጀል ሕጉ ጋር ካለው የመጣጣም ችግር ይመስላል፡፡ ሠራተኞች በቀጥታ ተግባር ለፈፀሙት ጥፋት በዋና ወንጀል አድራጊነት ተጠያቂ ከመሆን ይልቅ ሠራተኞች የፈፀሙት ጥፋት ሁሉ እንደመተባበር፣ መርዳትና መመሳጠር ስለተቆጠረ የፍሬ ነገር ዝርዝሩ የወንጀል ሕጉን መመዘኛ በሚያሟላ ሁኔታ ግልጽነት ያለው አይደለም፡፡ የዐ/ሕግ ምስክሮች ሲሰሙም ይህ የመተባበር፣የመርዳትና የመመሣጠር ሁኔታ ጥብጥ ሆኖ ሲያዝም ሆነ ሲመሰከር አያጋጥምም፡፡

## 6.2 የግል ባለሐብትን በተመለከተ

የግል ባለሐብቶችን በተመለከተ ደረሰኝ ወዲያውኑ አልሰጣችሁም በሚል ክስ የሚመሠረትባቸው አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 2/11/ እንደተሻሻለው አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀጽ 50/መ/2/ ተጠቅሶ ነው፡፡ አንቀጽ 2/11/ "ሰው" ለሚለው ቃል የተሰጠ ትርጉም ሲሆን አንቀጽ 50/መ/2/[81] ደግሞ "በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ "ግብይት ያከናወነ" ጥፋተኛነቱ በፍ/ቤት ሲረጋገጥ ይቀጣል በማለት የሚደነግግ የጥፋት ድንጋጌ ነው፡፡

በግል ባለሐብት ላይ የሚጠቀሰውን የሕግ ድንጋጌ በተመለከተ የሚነሱ የሕግ መከራከሪያዎች አሉ፡፡ እነዚህም፣ አንቀጽ 50/መ/ለ/ በቀጥታ ግብይቱን ያከናወነ የግል ባለሐብት ሊከሰስበት የሚገባው ድንጋጌ ነው፣ ግብይቱን ያላከናወኑና በቦታውም ያልነበሩ የግል ባለሐብቶች ላይ ይህ ድንጋጌ ሊጠቀስ አይገባም፣በተለይ የአንቀጽ 50/መ/2/ ድንጋጌ የዋና ወንጀል አድራጊነት የወንጀል ተሣትፎ ዓይነትን የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ዓይነት ተጠያቂነት ያለው የሕግ ሰውነት ላላቸው ድርጅቶች እንጂ ለግል ባለሐብቶች አይደለም፡፡ የግል ባለሐብቱ ተመሣጥሮ ከሠራተኛው ጋር ድርጊቱን ፈጽሟል ከተባለም ሊከሰስ የሚገባው በተለያዩ ክስ ሣይሆን በወ/ሕ/ቁ. 32 መሠረት በግብረአበርነት አንቀጽ 50/መ/2/ ተላልፈሐል ተብሎ እንጂ በተለያዩ ክስ ሲሆን የሚችልበት የሕግ መሠረት የለም የሚሉ ክርክሮች በተከሣሾችና በጠበቆቻቸው በኩል ይቀርባሉ፡፡

---

[81] የአንቀጽ 2/11/ ሙሉ ድንጋጌ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ፣ የግል ባለሐብት፣ድርጅት፣ የጋራ ልማት ማኅበር ወይም የሰዎች ኅብረት ሲሆን፣ ሌላን ሰው በመወከል ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የንግድ ሥራ የሚያካሂድ የንግድ ወኪልን ይጨምራል፣ የሚል ነው፡፡ የ50/መ/2/ ሙሉ ድንጋጌ "መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል "የሚል ነው፡፡

በዐ/ሕግ በኩል የሚቀርበው መከራከሪያ ደግሞ "ሰው" ለሚለው ቃል የተሰጠው ትርጉም የግል ባለሐብትንም ስለሚጨምር፣ የግል ባለሐብቱ ደግሞ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት በሕጉ ላይ በግልጽ ስለተጠቀሰ፣ ድርጅቶችን በተመለከተ ሥራ አስኪያጁ ያለወንጀል ተሣትፎ ተጠያቂ እንዲሆን እየተደረገ የግል ባለሐብትን በተመለከተ ግን "ግብይቱን ካላከናወነ" ሲከሰስ አይገባውም ማለት የሕጉን አላማና ግብ የሚቃረን ስለሆነ በዚህ ረገድ የሚቀርበው መከራከሪያ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡[82]

ፍ/ቤቱም በተከሣሾች በኩል የሚቀርበውን መከራከሪያ መሠረት በማድረግ የግል ባለሐብቱን ከክስ ነፃ ያደረገበት ውሣኔ አያገኝምም፡፡ ይሁን እንጂ የግል ባለሐብቱ እንደሥራ አስኪያጁ ሁሉ ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ጥፋቱን እሱ እንደፈፀመ ይቆጠራል የሚል ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ የግል ባለሐብቱ ተጠያቂነት አከራካሪ መሆኑ አይቀርም፡፡ ለዚህ መሠረታዊ መፍትሔ የግል ባለሐብቱን ተጠያቂነት በግልጽና ለትርጉም ባልተጋለጠ ሁኔታ መደንገጉ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህ ደግሞ የሕግ ማሻሻያ ሁኔታዎች ሲታሰቡ እንደሚገባ የሚያመለክት ነው፡፡

### 6.3 ወኪልን በተመለከተ

በሁለት የወንጀል ክሶች ላይ በወኪሎቹ ላይ የተጠቀሰው አንቀጽ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 55 እና አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀጽ 50/ለ/1/ ተላልፈዋል የሚል ነው፡፡ አንቀጽ 50/ለ/1/ የተጠቀሰው ሁለቱም የግል ባለሐብቶች መሣሪያውን መጠቀም ስላልጀመሩ ነው፡፡ አንቀጽ 55 የተጠቀሰው የግል ባለሐብቱን ረድተዋል ወይም አበረታተዋል በሚል ነው፡፡ የውክልና ስልጣናቸውን በተመለከተ በክሱ ላይ የግል ባለሐብቱን ንብረት የማስተዳደር የውክልና ስልጣን እንዳላቸው ተጠቅሷል፡፡ በሁለቱም መዝገቦች ላይ የግል ባለሐብቶቹም ተከሰዋል፡፡

የውክልና ሰነዱን ይዘት ስንመለከት በአንደኛው ክስ ላይ ያለው ወኪል የንግድ ፈቃድ ቁጥሩ ተጠቅሶ፣ በግልጽ ድርጅቱን እንዲያስተዳድርና እንዲቆጣጠር ስልጣን ያልተሰጠው ሲሆን በደፈናው ግን ማናቸውንም የሚንቀሣቀስና የማይንቀሣቀስ ንብረት እንዲሸጥ እንዲለወጥና ለሶስተኛ ወገን እንዲያስተላልፍ የሚል የውክልና ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በሁለተኛው መዝገብም ወኪሉ የተሰጠው ስልጣን ከዚሁ ጋር ተመሣሣይ ነው፡፡[83] በሌላ ወኪል ላይ ተመሣሣይ ሕግ ተጠቅሶ በቀረበ 3ኛ ክስ ላይ ደግሞ ለወኪሉ የተሰጠው የውክልና ስልጣን የንግድ ፈቃድ ቁጥር፣ የዋና ምዝገባ ምስክር ወቀት ቁጥርና የንግድ ዘርፉ ተመዝግቦ ነው፡፡ በዚህ መዝገብ[84] ላይ ወካዩ አልተከሰሰም፡፡

የታክስ አዋጁ ወኪል ማለት በሌላ ሰው ስም የሚሠራ ማናቸውም ሰው ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ በመርህ ደረጃ የውክልና ስልጣን በጠባቡ ሊተረጉም የሚገባው ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተወካዩ አንድን ድርጅት እንዲቆጣጠርና እንዲያስተዳድር ወይም በሕጉ አነጋገር በወካዩ ትዕዛዝ እየሠራ እንደሆነ ተደርጐ ሲወሰድ የሚገባው በማንኛውም ጥቅል የውክልና ሰነድ መሠረት ነው ወይስ ድርጅቱን በሚመለከት በግልጽ በተጠቀሰ የውክልና ስልጣን መሠረት ነው የሚለው መሠረታዊ የሕግ ነጥብ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በግልጽ የንግድ መደብሩ በስም፣ በንግድ ፈቃድና በዋና ምዝገባ ሰርተፊኬት ቁጥር ተጠቅሶ እንዲያስተዳድሩና እንዲቆጣጠሩ ስልጣን የተሰጣቸው ወኪሎች የበለጠ ለተጠያቂነት የቀረቡ ሲሆን በዚህ መልክ የወከሉ ባለሐብቶችም በምርመራ ሒደት የድርጊት ተሣትፎ ያላቸው መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር አለመከሰሳቸው ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሶስተኛው ክስ የሕጉቹን መመዘኛ ያሟላ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

---

82 ፀሐፊው እነዚህን መከራከሪያዎች ለማወቅ የቻለው በችሎት ከሚደረጉ ክርክሮች ነው፡፡
83 ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁ. 192995 እና 183397፣181242
84 ከጠበቃ ጫንያለው እሹ፡ የተገኘ መረጃ

ዐ/ሕጐች በራሣቸው ለመወሰን ያላቸው ነፃነት ለዚህ ዓይነት ልዩነት እንዱ ምክንያት ሲሆን ይችላል:: ለምሣሌ አንዳንድ ዐ/ሕጐች ባለሐብቱ ወኪል ካለው ወኪሉም መክሰስ አለበት ብለው ሲያምኑ አንዳንዶቹ ደግሞ፣ ወኪል ከተከሰሰ ባለቤት ሲከሰስ አይገባም ብለው ያምናሉ:: አንዳንዶች ደግሞ የወኪል ተሣትፎና የተሰጠው የውክልና ስልጣን ዓይነት ከግምት ውስጥ ሲገባ ይገባል ይላሉ:: ማንኛውም ዐ/ሕግ በክስ አመሠራረት ላይ ያለው ነፃነት ተገቢውን ክብር ሊያገኝ የሚገባው ቢሆንም መሠረታዊ የሕግና የፍሬ ነገር ጉዳዮችን ታሣቢ ባደረገ ሁኔታ መሪ ደንቦችን የመከተል አሰራር ቢኖር ተገቢ ነው::[85] ከዚህ አንፃር በወንጀል ተሣትፎ ከሌላቸው በስተቀር በግልጽ ተመዝጋቢውን የንግድ መደብር እንዲያስተዳድሩና እንዲቆጣጠሩ የውክልና ስልጣን ከተሰጣቸው ድርጅቶች ውጪ በሌሎች ወኪሎች ላይ ክስ እንዳይመሠረት ጥንቃቄ ቢደረግ የተሻለ ነው::

## 6.4 ድርጅቶችን በተመለከተ

በአንድ ኩባንያ ላይ በተመሠረተ ክስ በኩባንያው ላይ የቀረበው ክስ ላይ የተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ "በወንጀል ሕግ አንቀጽ 34/1/ እና በተሻሻለው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 22 /1/[86] አንቀጽ 50/መ/2/ የተደነገገውን ተላልፏል የሚል ሲሆን በሌላ ኩባንያ ላይ በቀረበ ሁለተኛ ተመሣሣይ ክስ[87] ደግሞ ከላይ በመጀመሪያው ክስ ላይ የተጠቀሰው አንቀጽ 22/1/ ሣይኖር የተጠቀሰው አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀጽ 10/1/[88] ነው:: ይህ ድንጋጌ ደረሰኝ ወዲያውኑ መስጠት አለበት የሚል ድንጋጌ ሲሆን 22/1/ ደግሞ "ደረሰኝ መስጠት አለበት" በሚል የሚደነግገው አንቀጽ ነው::

የድርጅት ኃላፊነት ሲቋቋም የሚገባው በኃላፊዎች ወይም በሠራተኞች ጥፋት ላይ ተመስርቶ ነው:: ይህን የወንጀሉን ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር በተመለከተ በመጀመሪያው ክስ ላይ ሠራተኞቹ /3ኛ እና 4ኛ ተከሣሾች/ "<u>የድርጅቱ ሕግና ደንብን አክብር የመስራት ግዴታውን ጥሰዋል</u>" በሚል የተገለፀ ሲሆን በሁለተኛው ክስ ላይ ግን በደፈናው ሠራተኞች/3ኛ እና 4ኛ ተከሣሾች/ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚታተም ደረሰኝ ባለመስጠታቸው ያለሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ደረሰኝ ግብይት ማካሄድ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው:: ሁለቱንም ክሶች ስናነፃጽር የመጀመሪያው ክስ የወ/ሕ/ቁ. 34/1/ መመዘኛ ያሟላል:: ይኸውም ሠራተኞቹ ድርጅቱ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታውን ጥሰዋል በማለት ይገልፃል:: ሁለተኛው ክስ ግን ይህን ስለማይገልጽ የተሟላ አይደለም:: ለምን አላማ የድርጅቱን ግዴታ ጣሰ ለሚለው ግን ሁለቱም ክሶች የሚገልጹት ነገር የለም::

የሐሣብ ሁኔታን በተመለከተም ሆነ ተብሎ ሲፈፀም የሚገባው ተግባር እንደመሆኑ መጠን ሠራተኞቹ የድርጅቱን የሕግ ግዴታ የጣሱት ሆነ ብለው ስለመሆኑ በሁለቱም ክሶች ላይ አልተጠቀሰም:: ይሁን እንጂ ተግባሩን የፈፀሙት ለምን ለምን ዓላማ እንደሆነ ለምሣሌ በመንግስት የታክስ ጥቅም ላይ ጉዳት ከማድረስ በማሰብ ወይም ድርጅቱን ለመጥቀም ነው በሚል ባይጠቀስም ሆነ ብለው ለመፈፀማቸው ግን ሊጠቀስ ይገባል:: የወንጀል ተሣትፎአቸውን በተመለከተ በጀመሪያው ክስ መደምደሚያ ላይ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከሰዋል የሚል ሲሆን በሁለተኛው ክስ ላይ ግን ምንም የተጠቀሰ የተሣትፎ ዓይነት የለም:: ስለሆነም የመጀመሪያው ክስ ለ34/1/ መመዘኛ የቀረበ ሲሆን ሁለተኛው ክስ ግን ይህን

---

85 ከቀድሞው የባለስልጣኑ ዐ/ሕግ ጋር የተደረገ ውይይት/ስማቸው እንዲገለጽ ስላልፈለጉ አልተገለፀም/

86 የአንቀጽ 22/1/ ሙሉ ድንጋጌ ይመለከቷል::

87 ሁለቱም ኩባንያዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበራት ሲሆኑ፣ ድርጊቱ ሲፈፀም የሁለቱም ኩባንያ ሥ/አስኪያጆች በቦታው አልነበሩም፣ ሁለቱም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚጠቀሙ ኩባንያዎች ናቸው:: ስለሆነም ጉዳዮቹ ለንጽጽር የተመረጡት ይህንኑ መመሣሰል መሠረት በማድረግ ነው::

88 የአንቀጽ 10/1/ ሙሉ ድንጋጌ ይመለከቷል::

አያሚላም። የታክስ ሕጉን በመተላለፍ የሚቀርብ ክስ የወንጀል ሕጉንና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉን መመዘኛዎች አሟልቶ መቅረብ ያለበት ስለሆነ የሠራተኞቹ ድርጊትና የወንጀል ተሣትፎ እንዲሁም ድርጊቱ የተፈፀመበት የሒሣብ ሁኔታ የወ/ሕ/ቁ. 34/1/ እና ወ/ሕ/ቁ. 23/2/ መሠረት አድርጐ ሊቀርብ ይገባል።

## 6.5 ሥራ አስኪያጅን በተመለከተ

በሁለት የተለያዩ ኩባንያዎች ሥራ አስኪያጆች ላይ የቀረበ ክስን ስንመለከት በአንደኛው ክስ ላይ በሥራ አስኪያጁ ላይ የተጠቀሰው አንቀጽ የወንጀል ሕግ ቁ. 32/1/ለ/ እና በ94 ዓ.ም የወጣውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 56/1/ የተሻሻለው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀጽ 50/መ/2/ በመተላለፍ የሚል ሲሆን በፍሬ ነገር ዝርዝሩ ደግሞ የመቆጣጠርና የማስተዳደር ኃላፊነታቸውን አልተወጡም የሚል ነው፡፡[89]

በሁለተኛው ክስ ደግሞ የወ/ሕ/ቁ. 32/1/ለ/ ካስመጠቀሱ ውጪ በሌላው የተጠቀሰው ሕግ ተመሣሣይ ሆኖ የፍሬ ነገር ዝርዝሩ "ሥራ አስኪያጅ ድርጊቱን እንደፈፀመ ስለሚቆጣር፣ ከመሣሪያው የታተመ ደረሰኝ ባለመስጠት ወንጀል ተከሷል" ይላል። በአንዳንድ ክሶች ላይ ደግሞ የወ/ሕ/ቁ. 34/1/ ይጠቀሣል። ከላይ የተመለከቱት ሁለቱ ክሶች ግን የወ/ሕ/ቁ. 34 መሠረት ያደረጉ አይደለም። የወንጀል ተሣትፎን በተመለከተ የመጀመሪያውን ክስ 32/1/ለ/ መሠረት በማድረግ የተሣትፎ ዓይነቱን ሲገልጽ የሞከረ ቢሆንም ይህ አንቀጽ ከአንቀጽ 56/1/ ጋር ካለው አለመጣጣም የተነሣ በክሱ ዝርዝር ላይ በግልጽ አልተጠቀሰም። 2ኛው ክስ ግን በደፈናው የ56/1/ ድንጋጌ ብቻ ያሰፈረ ነው። በአንዳንድ ክሶች ላይ ደግሞ የሥራ አስኪያጅ ተጠያቂነት የድርጅት ተጠያቂነት ውጤት ነው በሚል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1/ ይጠቀሣል። በአጠቃላይ ይህ ችግር የሚታየው የወንጀል ሕጉን ከታክስ አዋጆቹ ድንጋጌዎች ጋር አጣጥሞ ለመሔድ ካለው ችግር የተነሣ ስለሆነ የታክስ ሕጎቹን ድንጋጌ ከወንጀል ሕጉ ጋር አጣጥሞ ለማስኬድ የሚያስችል የሕግ ማሻሻያ ሥራዎች ሊኖሩ እንደሚገባ የሚያሣይ ነው፡፡[90]

## 7. የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ይዘት

እንደማንኛውም የወንጀል ክርክር ከሣሽ የሆነው የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ ያቀረበውን ክስ በማስረጃ የማስደገፍ ግዴታ አለበት። ዐ/ሕግ በማስረጃነት ሊያቀርብ የሚችለውን የማስረጃ ዓይነት በተመለከተ የተለየ የማስረጃ ደንብ ስለሌለና ተፈፃሚነት ያለውም የሥነሥርአት ሕግ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርአት ሕጉ ስለሆነ ይህንኑ መሠረት አድርጐ ይጠቅመኛል የሚለውን ማንኛውንም ማስረጃ ማቅረብ ይችላል።[91] በዚህ መሠረትም ዐ/ሕግ ምስክርና የሰነድ ማስረጃዎች በማስረጃነት ያቀርባል። ይሁን እንጂ የሚቀርበው ማስረጃ በአብዛኛው ተመሣሣይነት ያለው ነው። በተለይ ምስክሮቹ በጉምሩክና ገቢዎች ባለስልጣን የክትትል ቡድን አባላት ስለሆኑ በአብዛኛው ታስቦበትና ታቅዶ በሚደረግ ክትትል ወይም በድንገተኛ ክትትል ወቅት ያጋጠማቸውን የሚመሰክሩ ምስክሮች ስለሆኑ የምስክር ማስረጃው ጠቅለላ ይዘት ተመሣሣይነት ያለው ነው። በሰነድ ማስረጃ ረገድም ተመሣሣይነት ይታያል። ስለሆነም የሁለቱንም ማስረጃዎች ይዘት እንደሚከተለው እንመለከታለን።

---

89 በፌ/የመ/ ደ/ ፍ/ቤት የመ/ቁ. 183174

90 በዚህ ረገድ በአጠቃላይ የታክስ ሕጐቻችን ያለባቸው ችግር በጥልቀት ስመረዳት አቶ ታደሰ ሌንጮ በኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት 25ኛ ቮሊዩም ቁ. 1 ላይ The Ethiopian Tax System Cutting Through the Labyrinth and Padding the Gaps በሚል ርዕስ የፃፉትን ጥልቀት ያለው የምርምር ጽሑፍና ይህንኑ ጽሑፍ ተንተርሶ ሰኔ 3/2004 ዓ.ም በታተመው ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ የሰጡትን ቃለ ምልልስ ማንበቡ ይመከራል።

91 በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. ከ142-145 የተደነገጉትን ይመለከቷል።

## 7.1 ምስክሮች

በተግባር በሚደረጉ ክርክሮች በዐ/ሕግ በኩል ምስክሮች በማስረጃነት እየተቆጠሩ ይሰማሉ፡ ምስክሮቹም የራሱ የከሣሽ መ/ቤት ባልደረቦች የሆኑ አስቀድሞ በደረሰ ጥቆማ ወይም በድንገት ወይም ጥቆማ ባይኖርም በእቅድ በተያዘ ክትትል መሠረት የሚሰማሩ የባለስልጣን መ/ቤቱ ተቆጣጣሪዎች ሲሆኑ በማስረጃ ዓይነትነቱ ቀጥተኛ ማስረጃ (direct evidence) ሊባል የሚችል ነው:: አንዳንድ የታክስ ሕጐች የማስረጃ ደንቦችን ይዘዋል:: በእነዚህ የማስረጃ ደንቦች ላይ ተቀባይነት ስላላቸው ማስረጃዎች (admisible evidences) በግልጽ ተደንግጓል:: ለምሣሌ በተ.እ.ታ. ማሻሻያ አዋጅ ቁ. 609/2001 አንቀጽ 13/3/ ላይ በድንገተኛ ቁጥጥር የሚገኝ መረጃ ያለፍ/ቤት ትእዛዝ ሊያዝ እንደሚችልና በፍ/ቤትም በኩል ተቀባይነት እንዳለው ተደንግጓል:: ከዚህ አንፃር ደረሰኝ ከመስጠት ግዴታ ጋር በተያያዘ በፍ/ቤት ተቀባይነት ስላለውና ስለሌለው ማስረጃ የታክስ ሕጉ የተለየ ድንጋጌ አልያዘም:: በዚህ መሠረት በምስክርነት የሚቀርቡት የመ/ቤቱ ባልደረቦች ስለሚሰበስቡት ማስረጃና ስለማስረጃው ተቀባይነት የሚደነግገው የተለየ የማስረጃ ደንብ የለም:: ምስክሮቹ ቀርበው ሲመሰክሩም የሚመሰክሩት ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ጊዜና ቦታ እንደነበሩ፣ ስራቸውም የከሣሽ መ/ቤት ባልደረባ እንደሆኑና በቦታው በነበሩበት ጊዜ ከተመዝጋቢው ድርጅት እቃ ወይም አገልግሎት ገዝተው ወይም አገልግሎት ተጠቅመው ደረሰኝ እንዳልተሰጣቸው በመመስከር የዐ/ሕግን ክስ የሚያስረዱ ናቸው:: ዐ/ሕግ ምስክሮቹ ቀርበው ምን እንደሚመሰክሩ ጭብጥ ሲያሲዝ የሚያስመዘግበው ጭብጥ በአብዛኛው ይህንኑ ነው::

ደረሰኝ አለመስጠትን በተመለከተ በሚቀርቡ የወንጀል ክሶች ዐ/ሕግ ሌሎች ምስክሮችን አቅርቦ ያስመሰከረበት አጋጣሚ የለም:: ለምሣሌ በቦታው የነበሩ ሌሎች ገዥዎች ወይም አገልግሎት ተጠቃሚዎች በወቅቱ ስለተመለከቱት ሁኔታ እንዲመሰክሩ ሲባል በምስክርነት ተቆጥረው ቀርበው እንዲመሰክሩ የተደረገበት ጉዳይ የለም ለማለት ይቻላል:: በዚህ ምክንያት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት እራሱ ምርመራ የሚያጣራ፣ እራሱ ከሣሽ ፣እራሱ ምስክር መሆኑ ተገቢ አይደለም በሚል በጠበቆች የሚቀርቡ መከራከሪያዎች አልፎ አልፎ ያጋጥማሉ::[92] ምክንያታቸውም እንደዚህ ዓይነት ምስክሮች ለምስክርነት የሚመጡት አስቀድመው ተከሣሽ ጥፋተኛ ነው የሚል ሐሣብ በጭንቅላታቸው ይዘው ስለሆነ፣ እውነቱን ለመመስከርም የከሣሽ መ/ቤት ባልደረባ ስለሆነ በስራቸው ላይ መጥፎ ውጤት ሊከተል ይችላል በሚል ፍርሐት ያዩትንና የሰሙትን፣ እንዲሁም በነፃ ህሊናቸው የተገነዘቡትን በትክክል ለፍ/ቤቱ ይመሰክራሉ ተብሎ አይታመንም፣ በአጠቃላይ እንደዚህ አይነት ምስክሮች ገለልተኛ ናቸው ተብሎ ለማመን አስቸጋሪ ስለሆነ ነው የሚል ነው::

በተቃራኒው ምስክሮቹ የሚመሰክሩበት ጉዳይ አስቀድሞ በተገቢው ክትትል የተደረሰበት ፍሬ ነገር ስለሆነ፣ የመንግስት ሠራተኛ መሆናቸውም በቀላሉ ሊታመኑ የሚገባ እንደሆኑ ያሣያል፣ ተከሣሽም በራሱ በኩል ምስክሮችን አዘጋጅቶ ለማቅረብ እድል ስላለው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ገለልተኛ የሆነን ሰው ለማስመስከር አስቸጋሪ ስለሆነና እንደ እንግሊዝ ያሉ ሐገሮችም ጭምር የታክስ ሰርቪሳንስ ሠራተኞቻቸውን በዚህ መልክ ማስመስከር የተለመደ ስለሆነ፣ እንዲሁም የሥነሥርአት ሕጉ በዚህ መልክ ምስክሮችን ማሰማት ስለማይከለክል መቃወሚያው ተገቢ አይደለም የሚል መከራከሪያ በባለስልጣኑ ባለሙያዎች በኩል ይቀርባል::

በሌላ በኩል ከምስክርነቱ አሰማም ጋር በተያያዘም አልፎ አልፎ የሚታዩ አከራካሪ ሁኔታዎች አሉ:: የዐ/ሕግ ምስክሮች የፍሬነገር ምስክር ናቸው ከተባለ በኋላ እንደባለሙያ ምስክር ሆነው ሲመሰክሩ ያጋጥማል:: ለምሣሌ በብዛት የሚያጋጥመውን ለማንሣት ለምን ደረሰኝ ይሰጠን

[92] ለምሣሌ አንድ ጠበቃ ይህን መከራከሪያ በችሎት ሲያቀርቡ ፀሐፊው ሰምቷል:: ፍ/ቤቱ ይህን መከራከሪያ እንደማይቀበለው ስለሚያውቅ ፀሐፊው በያዛቸው ጉዳዮች ይህን ክርክር አንስቶ አያውቅም:: መከራከሪያው ምክንያታዊነት ሊኖረው ቢችልም ባለስልጣን መ/ቤቱ በሕግ የተሰጠውን ግልጽ ስልጣን ወደጐን በመተው ፍ/ቤቱ ሊያደርግ የሚችለው የተለየ ነገር የለም:: ፍ/ቤቱ የግድ የባለስልጣን መ/ቤቱን ስልጣን ማክበር ይኖርበታል::

ብላችሁ አልጠየቃችሁም? በሚል በተከሣሾች ወይም /በጠበቃቸው/ ሲጠየቁ ደረሰኝ የመጠየቅ ግዴታ የለብንም በማለት ይመልሣሉ። በምን ምክንያት ሲባሉ "ሕጉ ስለማይል" በማለት ይመልሣሉ፣ ከዚህ በኋላ ሕጉን ያውቁታል ወይ? ወዘተ የሚል ጥያቄ ሲቀጥል ምስክራችን የሙያ ምስክር ስላልሆኑ ይህን ጥያቄ ሲጠየቁ አይገባም በሚል ዐ/ሕግ ስለሚቃወም ፍ/ቤቱ እንዳይጠየቅና የተጠየቀው ጥያቄም እንዳይመለስ ይከለክላል።[93] የከሣሽ ወገን ምስክርነት፣ የህፃናት ምስክርነትና የሙያ ምስክርነት ጉዳዮች ላይ አንዳንድ አገሮች መሪ ደንቦችና ዝርዝር የስነስርአት ሕግ አላቸው። በዚህ ረገድ ካናዳ አንዷ ተጠቃሽ አገር ነች።[94] ይሁን እንጂ የስነስርአት ሕጋችን ግልጽ ድንጋጌ ስለሌለው ዐ/ሕግ ከላይ በተመለከተው ሁኔታ የራሱ መ/ቤት ባልደረቦች ቀርበው ሲመሰክሩ አይገባም የሚለው መቃወሚያ የሕግ መሠረት የለውም። የተከሣሽ ንጹህ ሆኖ የመገመት መብት እንዳይጐዳና አላግባብ እንዳይወነጀል ግን ፍ/ቤቱ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል።

### 7.2 የሰነድ ማስረጃዎች

ዐ/ሕግ በሚመሠርታቸው ክሶች ላይ የሰነድ ማስረጃዎችን ያቀርባል። ክስ የሚመሠረትባቸው ድርጅቶችና የግል ባለሐብቶች የተ.እ.ታ. ተመዝጋቢዎች ስለሆኑ ይህንኑ የሚያረጋግጠውን የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የንግድ ፈቃድ፣ ተከሣሽ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ከሆነም የመተዳደሪያና የመመስረቻ ጽሑፉ በማስረጃነት ተያይዞ ይቀርባል። ወኪል በተከሰሰበት ጉዳይ ደግሞ ለወኪሉ የተሰጠው የውክልና ስልጣን ማስረጃ በሰነድ ማስረጃነት ተያይዞ ይቀርባል። በዐ/ሕግ ያቀረበው ክስ ተመዝጋቢው መሣሪያውን መጠቀምና ከመሣሪያው የወጣ ደረሰኝ መስጠት ሲገባው አልሰጠም የሚል ከሆነ ደግሞ ተከሣሽ መሣሪያውን እንዲጠቀም ግዴታ ያለበት መሆኑ የሚያሣይ የጋዜጣ ማስታወቂያ፣ በዚሁ መሠረት የሰጠው የደብዳቤ ማሳሰቢያ ካለም እሱንና እንዲሁም ደብዳቤ ሳይሰጠው በቤት ለቤት ቅስቀሳ የተነገረው ከሆነም እራሱ ተከሣሽ ወይም ሠራተኛው ይኸው ስለመደረጉ የፈረሙበት ሰነድ በማስረጃነት እንዲቀርብ ይደረጋል። እነዚህ ማስረጃዎችን መሠረት በማድረግ ተከሣሾች ደረሰኝ የመስጠት ግዴታቸውን ያልተወጡ መሆኑን ሰነዶቹ እንደሚያስረዱለት ዐ/ሕጉ ለፍ/ቤቱ ይገልፃል።

ስለሆነም የሚቀርቡት የሰነድ ማስረጃዎች በጥቅሉ የሚያስረዱት ተከሣሾች ያለባቸውን የሕግ ግዴታ እና ግዴታቸውን ያልተወጡ መሆናቸውን ነው። ይህ በአብዛኛው የሚታየውን የሰነድ ማስረጃ ይዘት ጥቅል ሁኔታ ለማሣየት እንጂ በሁሉም ክርክሮች ላይ የማስረጃ ዓይነትና ይዘት ፍጹም ተመሣሣይ ነው ለማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል። ለምሣሌ በአንዳንድ ክርክሮች ላይ ግብይት የተፈፀመበት ዕቃ በኤግዚቢትነት እንደተያዘ በማስረጃ ዝርዝር ላይ ይጠቀሣል። ይሁን እንጂ ይህን ማስረጃ በተመለከተ የሚነሣ ክርክር ስለሌለ ኤግዚቢቱ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ የሰጠበትና በዚህም መሠረት እንዲቀርብ የተደረገበት ሁኔታ የለም ለማለት ይቻላል።

የሰነድ ማስረጃዎቹን ተከትሉ በተከሣሾች በኩል የሚቀርብ መቃወሚያ ወይም መከራከሪያ ቢኖርም በአብዛኛው ለክርክር ያክል የሚቀርቡ እንጂ የሰነድ ማስረጃዎችን የሚያስተባብሉ አይደሉም። ይሁን እንጂ መቃወሚያው የሚቀርብበትና ፍ/ቤቶችም መቃወሚያውን የሚያስተናግዱበት ሥነ ሥርዓት ግን ከችሎት ችሎት ይለያያል። አንዳንዱ ችሎት በሰነዱ ላይ ያለ መቃወሚያ ከመደበኛው መቃወሚያ ጋር ከክስ መስማቱ በፊት እንዲቀርብ ሲያደርግ አንዳንዶቹ ደግሞ የዐ/ሕግ ምስክር ከተሰማ በኋላ ተከሣሽ ሲከላከል ይገባል ወይም አይገባም የሚለው ብይን ከመስጠቱ በፊት በሰነድ ማስረጃዎች ላይ ተከሣሽ አስተያየት

93 ፀሐፊው እራሱ በተከራከረባቸውና በችሎት ተቀምጦ የዐ/ሕግ ምስክር ሲሰማ በተከታተላቸው በርካታ ጉዳዮች ይህ ክርክር አጋጥሞታል።

94 David watt, watt's manual of criminal evidence,200:pp 5-24

እንዲሰጥበት ይፈቅዳሉ።[95] አንዳንዱ ችሎት ደግሞ በዐ/ሕግ የሰነድ ማስረጃ ላይ ተከሣሽ አስተያየት እንዲሰጥ የሚፈቅድ ወይም የሚያስገድድ ሥነ ሥርዓት የለም በማለት ተከሣሽ አስተያየት እንዳይሰጥ ይከለክላል። ይሁን እንጂ ተከሣሽ በአግባቡ የመከላከል መብቱ በሕገመንግስቱ ጥበቃ የተደረገለት መብት ስለሆነ በሰነድ ማስረጃዎች ላይ አስተያየት እንዲሰጥ መፍቀዱ ተገቢ ነው።

## 8. ስለተከሣሾች የመከላከያ ማስረጃ ይዘት

በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የታተመ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታችሁን አልተወጣችሁም በሚል የሚከሰሱ ተከሣሾች ሊያቀርቡት የሚችሉትንና እያቀረቡ ያሉትንም መከላከያ ማስረጃ በተመለከተ በሁለት የተከፈለ ነው። የድርጅት ሥራ አስኪያጅ የሆኑ ተከሣሾች ሊያቀርቡት የሚገባውን የመከላከያ ማስረጃ ይዘት የታክስ አዋጁ በግልጽ ስለደነገገ በዚሁ መሠረት እንዲያቀርቡ የሚጠባበቅባቸው ሲሆን ከእነሱ ውጪ ያሉ ተከሣሾች ግን ሊያቀርቡት የሚገባው መከላከያ እንደማንኛውም የወንጀል ተከሣሽ ነው። ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ጥፋት የሚቋቋመው ኃላፊነታቸው ወይም ሠራተኞቻቸው በሚፈጽሙት ጥፋት ላይ ተመስርቶ ስለሆነ እነዚህ ግለሰቦች የሚያቀርቡት መከላከያ ነፃ የሚያወጣቸው ከሆነ ድርጅቱም ነፃ ከሚወጣ በስተቀር ድርጅቱ ሊያቀርበው የሚችለው ራሣሱን የቻለ የተለየ የመከላከያ ማስረጃ የለም። ስለሆነም በሕግ የተገደበውን የመከላከያ ማስረጃ ይዘትና እንደማንኛውም የወንጀል ተከሣሽ ይጠቅመኛል በሚል ተከሣሹ ሊያቀርበው የሚችለውን ማስረጃ ይዘት እንደሚከተለው በሁለት ክፍለን እንመለከታለን።

### 8.1 ሠራተኞች፣ ባለሐብትና ወኪል ስለሚያቀርቡት መከላከያ

ሠራተኞችና ሌሎች ደረሰኝ ከመስጠት ግዴታ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በተከሣሽነት ሲቀርቡ በመከላከያ ማስረጃነት ሊያቀርቡ ስለሚገባቸው ጉዳዮች የታክስ ሕጎቹ የተለየ የማስረጃ ደንብ (rules of evidence) አልደነገጉም። በዚህ መሠረት መከላከያቸውን ሊያቀርቡ የሚገባቸው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሠረት ነው። የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ ተከሣሽ ይጠቅመኛል የሚለውን የሰነድና የሰው ማስረጃ፣ ፍ/ቤት እንዲያስቀርብለት የሚፈልገውን ማናቸውንም ማስረጃዎች ሊያስቀርብ እንደሚችል ስለሚፈቅድ የገደብ ወይም የክልከላ ድንጋጌ የለውም።[96] በተግባር በሚደረጉ ክርክሮችም ተከሣሽ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ተጠይቆ በተለያየ ምክንያት ፍ/ቤቱ ሲከለክለው አያጋጥምም። ተከሣሽ በራሱ ምክንያቶች የመከላከያ ምስክሮችን ማቅረብ ካልቻለም ሰፋ ያለ ጊዜ እና ተደጋጋሚ ቀጠሮ እየተሰጠው እንዲያቀርብ እድል ሲሰጠው ይታያል። ይህም ተከሣሽ የመከላከል መብቱን በአግባቡ እንዲጠቀም ስለሚያስችለው የሚነቀፍበት ምክንያት የለም። ይሁን እንጂ ጉዳዩ ውስብስብነት የሌለው ከመሆኑና በጥብቅነት የሚያዘው ነጥብ የተወሰነ ፍሬ ነገር ላይ የሚያጠነጥን ስለሆነ በአብዛኛው ተከሣሾች የሚያቀርቡት የመከላከያ ማስረጃ ምስክሮችን ነው። የሰነድ ማስረጃዎችን በተመለከተ የሚቀርቡበት አጋጣሚ በጣም ውስን ነው። ይህ የሚሆንበት ምክንያትም በተለያዩ ሁኔታ ገደብ ስላለ ሳይሆን ከክርክሩ ባህሪ የተነሣ የሰነድ ማስረጃ አስፈላጊነት እምብዛም ስለሆነ ነው።

የመከላከያ ምስክሮቹ የሚመሰክሩበት ጭብጥም ተመሣሣይነት ያለው ነው። ግብይቱ በተደረገበት ጊዜና ቦታ የነበሩ ሠራተኞችና ሌሎች ሰዎች የሚያነሱት መከላከያ ግብይቱ በተደረገበት ጊዜና ቦታ ነበርኩ፣ የከሣሽ መ/ቤት ነን ያሉ ገዥዎች እቃውን ከገዙ ወይም አገልግሎቱን ከገዙ በኋላ ገንዘቡን ጠረንጴዛ ላይ አስቀምጠው ደረሰኝ ሣይወስዱ ወጡ፣

---

[95] ፀሐፊው በተለያዩ ችሎቶች በተጠቀሱት የሥነሥርዓት ሁኔታዎች ተስተናግዷል። ተከሣሽ በማስረጃዎቹ ላይ አስተያየቱን እንዲሰጥ የሚፈቅዱ ችሎቶች የተከሣሽን የመከላከል ሕገመንግስታዊ መብት በማስከበር ረገድ የሚከተሉት ሥነ ሥርአት ተገቢ ስለሆነ ሊመሰገኑ ይገባል።

[96] የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 142-145 ይመለከቷል።

ገንዘቡን ከሰጡ በኋላ ደረሰኝ ጠብቁ እየተባሉ ዝም ብለው ወጡና ተመልሰው መጡ፣ ወረፋ ስለነበር ደረሰኝ እየተሰራላችሁ ስለሆነ ጠብቁ እየተባሉ ወጡና ተመልሰው መጡ፣ መሣሪያው ለጊዜው አልሠራም ብሎ ነበር፣ ካሸሬም ገንዘቡን አልቀበልም ብላ፣ ግዴለም ደረሰኝ እንፈልግም ካሏት በኋላ ወጡና ተመልሰው ገብተው አቁሚ አሏት፣ ሐዘን ላይ ስለነበርን ሱቅ አልከፈትንም ነበር፣እቃ ለመውሰድ ወደሱቅ ስንሔድ፣ካልሸጣችሁንል አሉ፣እኔ ሰራተኛ ስላልሆንኩ አልሸጥም፣ሱቁን ለመጠበቅ ነው የተቀመጥኩት፣ ሻጯ እስክትመጣ ጠብቁ እያልኳቸው አንችኩላለን ብለው ሲያጣድፉኝ ሸጥኩላቸው፣ የመሸጫ ኮድ እየታየ እቃዎች ማሽኑ ላይ እስከምመታ ጊዜ ይወስዳል፣ ኮድ እየታየ ሲመታላቸው ሲል አቁሚ ብለው አስቆሙን፤የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው በወቅቱ እየተበላሸ አስቸግሮን ስለነበር ወዲያውኑ ደረሰኝ ቆርጠን መስጠት አልቻልንም ነበር፣ አንሸጥም እያልን ገዥዎቹ ካልሸጣችሁልን ብለው ስለጉተጉቱን ነው የሸጥንላቸው[97] ወዘተ በሚሉ የመከላከያ ጭብጦች ዙሪያ የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው ያሰማሉ፡፡

በአጠቃላይ የመከላከያ ጭብጡ መሠረታዊ ነጥብ ደረሰኝ ወዲያውኑ ያልተሰጠበትን ምክንያት ማስረዳት ነው፡፡ ወኪሉም ግብይት አልፈፀምኩም፣ በቦታው አልነበርኩም ድርጅቱን የማስተዳድረውና የምቆጣጠረው እኔ አይደለሁም፣ እኔ መሐይም ነኝ፣ ስለማሽኑና ስለአሰራሩ የማውቀው ነገር የለም ወዘተ የሚል ነው፡፡በባለሐብት በኩል የሚቀርበው መከላከያም የተለያየ ነው፡፡ ግብይቱን እራሱ ያከናወነ ባለሐብት ከላይ የተመለከተውን ሠራተኞችና ሌሎች ተከሣሾች የሚያነሱትን የመከላከያ ነጥቦች ያነሣል፡፡ ግብይቱ ሲፈፀም ያልነበረ ከሆነ ደግሞ በቦታው ስላልነበርኩ ልጠየቅ አይገባም የሚል መከላከያ ያነሣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የድርጅት ሥራ አስኪያጅ እንደሚያነሣው መከላከያ ዓይነት ደረሰኝ ሣይቀበሉ አይክፈሉ የሚል ማሳሰቢያ ለጥፌአለሁ፣ ካሸር ስልጠና እንዲወስድ አድርጌአለሁ፣ ሠራተኞች ያለደረሰኝ ቢሸጡ ኃላፊነቱ የራሳቸው እንደሆነ አስፈርሚአለሁ በማለት በአዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 56/3/ መሠረት የተደነገጉትን መከላከያዎች የሚያስረዱ አሉ፡፡ ነገር ግን ይህ አይነት ተገቢውን የአሰራር ጥበብ መከላከያ በግልጽ የሥራ አስኪያጁ መከላከያ ተደርጐ የተደነገገ እንጂ የግል ባለሐብት በመከላከያነት ሊያነሳ የሚችለው ስላልሆነ በመከላከያነት ሊያገለግል የሚችል አይደለም በሚል የሚከራከሩ ባለሙያዎች አሉ፡፡

በሌላ በኩል ደረሰኝ ከመስጠት ግዴታ ጋር በተያያዘ የግል ባለሐብትና ድርጅት ያለባቸው ግዴታ ተመሣሣይ ስለሆነ ተገቢውን የአሰራር ጥበብ የተከተለ ባለሐብት ይህንኑ እንዳያስረዳ ሊከለከል አይገባም በሚል የሚከራከሩ አሉ፡፡ ይህ መከራከሪያ ምክንያታዊነት ያለው መከራከሪያ ነው፡፡ ድርጊቱን እራሱ ያልፈፀመ የግል ባለሐብት ዋና መከላከያው የሚሆነው ድርጅቱ ሕጋዊ ግዴታውን በአግባቡ እንዲወጣ በሚያስችለው የአስተዳደር ስርአት መሠረት እያስተዳደረው መሆኑን ማስረዳት እንደሆነ የድርጅት ኃላፊነት ጽንሰሐሣብ ላይ የተደረጉ ጥናትና ምርምሮች ያስረዳሉ፡፡[98] ይህ መሠረታዊ አስተሳሰብ ከላይ ለተመለከተው የግል ባለሐብት መከላከያም ተፈፃሚ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህን መከላከያ ለግል ባለሐብቱ አለመፍቀድ ተመሣሣይ ግዴታ ያለባቸውን ተመዝጋቢዎች በተለያየ የመብት አያያዝ ማእቀፍ ውስጥ እንዲካተቱና ሥራ አስኪያጁ የተሻለ የመከላከል እድል ሲኖረው ተመሣሣይ ጥንቃቄ ያደረገ የግል ባለሐብት ጥንቃቄው ዋጋ ቢስ ሆኖ በወንጀል እንዲቀጣ ስለሚያደርገው አድሉአዊ ውጤትን ያስከትላል፡፡ ይህ ደግሞ የሕጉ አላማ ነው ተብሎ አይታሰብም፡፡

በመከላከያ ምስክርነት የሚቀርቡትን ሰዎች ማንነት በተመለከተም የተለያየ ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ በወቅቱ እንደማንኛውም ገዥ በቦታው የነበሩ፣ ሌሎች የሽያጭ ሠራተኞች፣

---

97 ፀሐፊው የከሣሾች የመከላከያ ምስክሮቻቸውን ሲያሰሙ በችሎት ውስጥ ተቀምጦ ከሰማውና ማስታወሻ ከያዘበት በርካታ ጉዳዮች እንዲሁም እራሱም በጠበቃነቱ ካስመዘገባቸው ጭብጦችና ካሰማቸው የመከላከያ ምስክሮች ቃል ይህን ሁኔታ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

98 ለምሣሌ : Jonathan herring: Criminal law; 5th ed ( palgrave macmillan, new York,2008) :pp109-128 ያለውን ማንበቡ ይመከራል

የሽያጭ ሠራተኛ ብቻ በተከሰሰበት ደግሞ ካሸር የነበረ፣ በቦታው የነበረ ማንኛውም ሰው ወይም የሆነውን ነገር ሰማሁ ወይም እገሌ ነገረኝ የሚል የሰሚ ሰሚ ምስክር በመከላከያ ምስክርነት ይቀርባል፡፡ በፍ/ቤቱ በኩል ሲመዘን ግን በአብዛኛው የመከላከያ ምስክሮች ቃል እርስ በርሱ ይቃረናል፣ ደረሰኝ ያልተሰጠበት ምክንያት በቂ መሆኑን አላስረዱም፣ ምስክርነታቸው በመጠናናት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ እምነት የሚጣልበት አይደለም ወዘተ በሚሉ ምክንያቶች ውድቅ ይደረጋል፡፡[99] በዚህ ሁኔታ የሚደረገው የማስረጃ ምዘና ሙሉ በሙሉ የፍ/ቤቱ ስልጣን ነው፡፡ ተከሣሽ ማስረጃው የተመዘነው አላግባብ ነው የሚል ከሆነ ይግባኝ ማቅረብ መብቱ ነው፡፡

## 8.2 ሥራ አስኪያጅ ስለሚያቀርበው መከላከያ

ሥራ አስኪያጅ ስለሚያቀርበው መከላከያ አዋጅ ቁ. 285/94 በአንቀጽ 56/3/ ሀ/ለ/ ላይ የገደብ ድንጋጌ አስቀምጧል፡፡ በዚህ መሠረት ጥፋቱ ሲፈፀም ሥራ አስኪያጁ ሳያውቅ ወይም ሣይስማማ ብቻ ከሆነ፣ ጥፋቱን ለመከላከል ተገቢውን ትጋት እና የአሰራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ሣይወስድ አለመሆኑን ማስረዳት ይገባዋል፡፡ ይህን ማስረዳት ካልቻለ የወንጀል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ በ"ሀ" እና በ"ለ" ላይ የተጠቀሱት ገደቦች በአማርኛው ክፍል በ"እና" አለበለዚያም በ "ወይም" የተያያዙ አይደሉም፡፡ እንግሊዝኛው ግን "እና" በሚል አብረው (cumulatively) መሟላት ያለባቸው የገደብ መመዘኛዎች እንደሆኑ ይጠቅሣል፡፡

እነዚህ የገደብ ጥንቃቄዎች አንዳንድ ጊዜ አከራካሪ የሕግ ጉዳዮችን ያስነሣሉ፡፡የመጀመሪያው ሥራ አስኪያጁ አስቀድሞ በሕግ ያልተጣለበት ግዴታ፣ በመከላከያ እንዲያስረዳ መደረጉ ተገቢ ነወይ? የሚልና በ"ሀ" እና በ"ለ" የተጠቀሱት ገደቦች በ"እና" ያልተያያዙ ስለሆነ፣ እንዲህ በሆነ ጊዜ ሕጉ ሲተረጎም የሚገባው ተከሣሹን በሚጠቅም መልክ ስለሆነ ጥፋቱ ሲፈፀም፣ ሥራ አስኪያጁ ሣያውቅ ወይም ሣይስማማ የተፈፀመ ከሆነ ሥራ አስኪያጁ በሐላፊነት ሊጠየቅ አይገባም በሚል የሚከራከሩ አሉ፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ሕግ ላይ በሰጠው ትርጉምን የሚመለከት ውሣኔ ገደቦቹ በአንድነት መሟላት እንዳለባቸው አድርጐ የተረጐመው ሲሆን በ"ለ" ላይ የተቀመጠውን ገደብን በተመለከተም "--- ገዥዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ወዲያውኑ እንዲያገኙ የሚያስችል አሠራር መዘርጋት ሲገባቸው ይህንን በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ ባለማክበር - - - " በሚል ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ይህ ግዴታ በየትኛው ሕግ መሠረት የሥራ አስኪያጁ ግዴታ ሆኖ እንደተደነገገ ግን በውሣኔው ላይ አልተጠቀሰም፡፡

ይሁን እንጂ ከድርጅቶች የወንጀል ኃላፊነት ጋር በተያያዘ የሥራ አስኪያጆች ወይም የሌሎች ኃላፊዎች ተጠያቂነት ተገቢውን ጥንቃቄ ከመውሰድ ጋር የተያያዘ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡[100] አልፎ አልፎ አከራካሪ እየሆነ ያለው ሊወሰዱት የሚገባው የጥንቃቄ እርምጃ አስቀድሞ በሕግ ላይ ሊደነገግ ወይም ሊመለከት ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ነው፡፡ ይህም ቢሆን በአዋጅ ቁ. 609/2001 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 47/9/ሐ ላይ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ጥቅም ላይ በሚውለበት የንግድ ሥራ ቦታ "ደረሰኝ የማይሰጥ ከሆነ አይክፈሉ" የሚል ጽሑፍ ያለበት ማስታወቂያ መለጠፍ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

---

[99] ለምሣሌ በ06/10/2004 ዓ.ም በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት 1ኛ ወንጀል ችሎት የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ ይመለከቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፀሐፊው በዚህ መልክ የተሰጡ ፍርዶች ሲነበቡ በችሎት ተቀምጦ አዳምጧል፡፡

[100] በዚህ ጉዳይ ጠበቃ የነበረው አቶ ጫንያለው ሊላው ደንበኛው ሠራተኛውን አስፈርሞ ግብር ከሚከፈልበት ማኅደር ጋር እንዲያያዝለት ሲጠይቅ ተከልክሏል፡፡ ይህን ያደረገነው ደንበኛው በሠራተኞቹ ጥፋት ቢከሰስ ያስፈረሙበት ሰነድ ከግብር አስገቢው ማኅደር እንዲቀርብ ስለሚደረግ የሰነድን ታማኝነት ለማረጋገጥ አስቦ ነው፡፡ ተመዝጋቢዎች ይህን አይነት ጥረት ካደረጉ ሊበረታቱና ሰነዱም ከግብር ማኅደሩ ጋር ሊያያዝ ይገባል፡፡

ይህ መከራከሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደሥራ አስኪያጁ መከላከያ ስንመለስ በአንዳንድ ክርክሮች ሥራ አስኪያጅ ሠራተኞች ያስደረሰኝ ቢሸጡ ኃላፊነቱ የራሣቸው እንደሆነ ካስፈረሙ፣ ደረሰኝ ሣይሰጥዎ አይክፈሉ የሚል ማሳሰቢያ ከሰጠ፣ በመሣሪያው ላይ የተመደበ ሰራተኛ ስልጠና እንዲወስድ ካደረጉ ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል በሚል በነፃ እንዲሰናበቱ ይሆናሉ፡፡ ይሁን እንጂ በሴላ በኩል ሠራተኛቸውን ያስፈረሙበትን ሰነድ በመከላከያ ማስረጃነት ከሰጡ በኋላ ክክስ ወዲህ ያስፈረማቸሁት ነው፡፡[101] በሚልና ደረሰኝ ሳይሰጥዎ አይክፈሉ የሚለውን ማሳሰቢያ እንዳልተሰጠ በዐ/ሕግ ምስክሮች በማያጠራጥር ሁኔታ ተመስክሯል በማለት ውድቅ ተደርጉ ተገቢውን የእስራር ጥበብ ሥራ ላይ አላዋልክም በሚል ጥፋተኛ የተባሉ በርካታ ሥራ አስኪያጆች አሉ፡፡ ሥራ አስኪያጆችና የግል ባለሐብቶች በዚህ ረገድ ሲያደርጉት ስለሚገባው የጥንቃቄ እርምጃ ያለው ግንዛቤ በጣም አነስተኛ ስለሆነ ከፍተኛ ሥራ ሊሰራ እንደሚገባው ግልጽ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ መስጠት ግዴታ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን ተከትሎ የመጣ ግዴታ ነው፡፡ ይህ ግዴታ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በርካታ የወንጀል ክሶች የተመሠረቱ ቢሆንም በርግጠኝነት የቁጥሩን መጠን መናገር ግን አይቻልም፡፡ ክሶቹ ከተመሰረቱ በኋላ ክሱ ለተከሣሽ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ ክርክሩ እስከሚጠናቀቅ፣ ከዚያም በይግባኝ ደረጃ የሚነሱ በርካታ የሕግና የፍሬ ነገር መከራከሪያዎች አሉ፡፡ ከክርክሩ ባህሪ አዲስነት ጋር በተያያዘ እነዚህ መከራከሪያዎች ለውይይት ክፍት ሆነው የባለሙያ አእምሮ በሚገባ እንዲፈትሻቸው የተደረጉ ስለመሆኑ መረጃ ባይኖርም ለወደፊቱ ግን ሊፃፍባቸውና በነፃ አእምሮ ውይይት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች እንዳሉ ይታመናል፡፡

አሁን ባለው አዝማሚያ የታክስ ወንጀል ጉዳይ ትኩረትን የሚሻ ጉዳይ እየሆነ እንደሚቀጥል ይገመታል፡፡ ግብር ከፋዩ በቂ ግንዛቤ እየያዘ እራሱን እንዲጠብቅና መንግስትም የሚወስዳቸው እርምጃዎች ግብር ከፋዩን የሚያስጨንቁና የሚያሸማቅቁ ሆነው የኢንቨስትመንትና የንግድ እንቅስቃሴው እንዳይጉዳ አግባብ ያለው የታክስ ወንጀል አስተዳደር ሥርአትን ማስፈን ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ በቀናነት ከማሰብ ፣ከመተባበርና ሕጉን ለማስፈፀም በጋራ ጥረት ለማድረግ አንስቶ መሻሻል ያለበት ሕግ ካለም ከማሻሻል ውጪ የተሻለ አማራጭ የለም፡፡ ጽሑፉም የቀረበው እነዚህን ጉዳዮች ለማሣየትና በጉዳዩ ላይ ሐሣብ ለመለዋወጥ መነሻ የሚሆን ነገር ለመሰንዘር እንጂ ጽሑፉ በራሱ በጉዳዩ ዙሪያ እየተነሱ ያሉ ጉዳዮችን ጠቅላላ የዳሰሳና የተሟላ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመጠኑ ግን የክርክሩን ባህሪና ወደፊት ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ያሉ ስለመሆኑ ያመላከተ እንደሆነ ይገመታል፡፡

---

[101] ፀሐፊው በዚህ መልክ የተወሰኑ ውሣኔዎችን ለማግኘት ጥረት ቢያደርግም አላገኘም፡፡ በወረ ደረጃ ግን ነፃ የወጣ ሥራ አስኪያጅ እንዳለ ሰምቷል፡፡